# የባሃኢ ጸሎቶች

THE MANSION BAHJI · ACRE - ISRAEL

## የባሃኢ ጸሎቶች

ትርጉም:- የኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ
መንፈሳዊ ጉባኤ የትርጉም ኮሚቴ

የመልእክት ሣጥን ቁጥር 102
ስልክ:- 181372
አዲስ አበባ



አሳታሚ :-የኢትዮጵያ ባሃኢዎች
ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤ
የኅትመት ቦርድ

የመጀመሪያ ኅትመት 1984 ዓ.ም.
የተሻሻለ 2ኛ ኅትመት 1996 ዓ.ም.

# ማ ው ጫ


| አርእስት | ቁጥር | ገጽ |
|---|---|---|
| ጥቅሶች:- ..... በባሃአላህ............... | | 11 |
| ሀ) ልዩ ልዩ ጸሎቶች .......... | | 13 |
| የማለዳ : ................................... | | 13 |
| በባሃአላህ.... | 1...... | 13 |
| የጥዋት : ................................... | | 14 |
| በባሃአላህ..... | 2-3.... | 14 |
| የማታ : ................................... | | 15 |
| በባሃአላህ..... | 4-5..... | 15 |
| በአብዱል ባሃ | 6..... | 16 |
| የጋብቻ : ................................... | | 17 |
| በባሃአላህ..... | 7-8..... | 17 |
| በአብዱል ባሃ | 9..... | 18 |
| የፈውስ : ................................... | | 19 |
| በባሃአላህ.... | 10-15.... | 19 |
| ለስብሰባ : ................................... | | 24 |
| በባሃአላህ......... | 16.... | 24 |
| በአብዱል ባሃ.... | 17.... | 25 |


ርዕሶቹ፡ ጸሎቶቹን በቀላሉ ለማውጣት እንዲያመች ታስቦ የተሰጡ እንጂ፡ የቅዱሳት ጽሑፎቹ አካል አይደሉም። አብዛኞቹ ጸሎቶች ከተመደቡበት ርዕስ ውጪ ለሌሎችም ዓላማዎች ሊያገለግሉ ይችላሉ ።




| አርዕስት | ቁጥር | ገጽ |
|---|---|---|
| ለመንፈሳዊ ጉባኤ ስብሰባ:-. .................. | | 27 |
| በአብዱል ባሃ. | 18-20 | 27 |
| ለሕፃናት : ................................... | | 30 |
| በባሃአላህ.... | 21-22....... | 30 |
| በአብዱል ባሃ. | 23-26....... | 32 |
| ለወጣቶች : ................................... | | 33 |
| በአብዱል ባሃ... | 27-30 | 33 |
| የባሃኢ መዋጮ : ........................... | | 35 |
| ለመዋጮ ጸሎት: ........................... | | 36 |
| በአብዱል ባሃ..... | 31... | 36 |
| ለሙታን : ................................... | | 36 |
| በባሃአላህ......... | 32-33.. | 36 |
| በአብዱል ባሃ | 34.. | 40 |
| የቀብር ጸሎት: ........................... | | 40 |
| በባሃአላህ.. | 35.1-35.2.. | 40 |
| ለፈተናና ለችግር ጊዜ.: ...................... | | 43 |
| በባሃአላህ.... | 36.. | 43 |
| በባብ....... | 37.. | 44 |
| በአብዱል ባሃ | 38-39.. | 44 |

[illegible] 48
በአብዱል-ባሃ... 44.. 50

ጸሎተ ትምህርት:- ................................ 50
በባሃኦላህ....... 45-47.. 50
በአብዱል-ባሃ...48-51.. 52

የአቅኚዎች ጸሎት:- ............................ 57
በአብዱል ባሃ.. 52... 57

ለእምነቱ ድል:- .................................. 58
በባሃኦላህ....... 53-54.. 58
በባብ........... 55-56.. 60
በአብዱል-ባሃ.. 57-58.. 63

መንፈሳዊ ባሕርያትን ለማዳበር:- ............... 66
በባሃኦላህ....... 59-65.. 66
በአብዱል-ባሃ 66-69.. 70

ለሰው ዘር :- ...................................... 72
በባሃኦላህ....... 70.. 72
በባብ........... 71.. 72
በአብዱል-ባሃ.. 72-73.. 73

ለጥበቃ :- ........................................ 75
በባሃኦላህ....... 74-76.. 75
በባብ........... 77-80.. 76
በአብዱል-ባሃ.. 81-84.. 80



በባብ........... 88-89... 8
በአብዱል-ባሃ.. 90-91... 8

ለውዳሴና ለምስጋና:- ......................... 9
በባሃኦላህ...... 92-93.... 9
በባብ.......... 94.... 9
በአብዱል-ባሃ. 95.... 9

ለእርዳታ:- ...................................... 9
በባሃኦላህ....... 96.... 9
በባብ........... 97-98.... 9
በአብዱል-ባሃ.. 99-100... 10

ለአንድነት :- .................................. 10
በባሃኦላህ........101-102... 10
በአብዱል ባሃ... 103... 10

ከዓለማዊ ቁራኛነት ለመላቀቅ:- .............. 10
በባሃኦላህ....... 104-106.. 10
በባብ........... 107-108.. 10
በአብዱል-ባሃ.. 109.. 10

በአምላክ ቃል ኪዳን ለመጽናት:- .............. 10
በባሃኦላህ...... 110-111.. 10
በአብዱል-ባሃ. 112-114.. 11

[illegible] 114

በአብዱል ባሃ 119 121. 117

የእግዚአሔር እምነት እደ ሃይማኖቶች: ......... 120

ለእደ ሃይማኖቶች ጸሎት: ...................... 120

በባሃኦላህ........ 122.. 120

ለ) የግደታ ጸሎቶች

መግለጫ: በሾገ. ኢፊንዲ ስም ከተጻፈ ደብዳበ. (የመጀመሪያው አንቀጽ) 121

መግለጫ: በአብዱል ባሃ (ሁለተኛው አንቀጽ) 121

አጭሩ : ......................................... 121

በባሃኦላህ..... 123.. 121

መካከለኛው:- .................................. 122

በባሃኦላህ...... 124.. 122

ረጅሙ :- ....................................... 124

በባሃኦላህ...... 125.. 124

በየዕለቱ አንዴ 95 ጊዜ
የሚደገም ቃል:- ............................... 131

በባሃኦላህ..... 126.. 131






መልእክት ለአሕመድ:-......................... 132

በባሃኦላህ...... 127....... 132

መልእክተ እሳት:- .............................. 135

በባሃኦላህ...... 128....... 135

ረጅሙ የፈውስ ጸሎት:- ...................... 140

በባሃኦላህ..... 129....... 140

የቅዱሱ መርከበኛ መልእክት:-................. 147

በባሃኦላህ.... 130....... 147

የጉብኙት መልእክት ለባሃኦላህና ለባብ:-......... 155

በባሃኦላህ...131....... 155

የጥበቃ ጸሎት (መልእክት):-.................. 158

በባሃኦላህ..... 132....... 158

የዓመት ማሚያ (የአያሚ-ሀ) ቀናት ጸሎት:-... 159

በባሃኦላህ...... 133...... 159

የጾም ጸሎት:-.................................. 161

በባሃኦላህ...... 134...... 161

| አርእስት | ቁጥር | ገጽ |
|---|---|---|
| በጾም ጊዜ የማለዳ፡- ........................... | | 162 |
| በባሃኦላህ..... | 135 | 162 |
| የናውሩዝ (የአዲስ ዓመት) ጸሎት፡- ............ | | 168 |
| በባሃኦላህ..... | 136 | 168 |
| የጉብኝት ጸሎት የአብዱል-ባሃ፡- ............. | | 170 |
| በአብዱል ባሃ. | 137 | 170 |
| በጸሎት አማካይነት ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ እርምጃዎች፡-........................ | | 172 |
| የ19ኛ ቀን በዓላት የባሃኢ ወራት የመጀመሪያ ቀናት፡- .......... | | 175 |
| የባሃኢ አውደ ዓመታትና ክብረ በዓላት፡-....... | | 176 |




*የእግዚአብሔር ስም የተወሳበት፡ ምስጋናውም የተወደሰበት ሥፍራውም ፡ ቤቱም፡ ቢታውም ፡ ከተማውም፡ ልቡም ፡ ተራራውም ፡ መጠለያውም፡ ዋሻውም ፡ ሸለቆውም፡ ሀገሩም፡ ባሕሩም፡ ደሴቱም፡- ሜዳውም የተባረከ ነው።*

*አገልጋዬ ሆይ፡ የዝማሬህ ጥዑምነት የራስህን ነፍስ እንዲያቀጣጥልና የሁሉንም ሰዎች ልብ እንዲስብ፡ የተቀበልካቸውን የአምላክ ጥቅሶች፡ እነዚያ ወደ እርሱ የቀረቡት እንዳዘመሩት አዚማቸው። በአምላክ የተገለጹትን ጥቅሶች ማንም ሰው ብቻውን በክፍሉ ውስጥ ሆኖ ቢደግም፡ የፍጹም ኃያሉ አስራጭ መላእክት ከአፉ የሚወጡትን ቃላት መዓዛዎች፡ በሰፊው በሁሉም አቅጣጫ ያሠራጩዋቸዋል፡ የእያንዳንዱንም ትክክለኛ ሰው ልብ ትርታ እንዲጨምር ያደርጋሉ። ምንም እንኳ በመጀመሪያ ውጤቱን ባይገነዘበውም፡ የተሰጠው ጸጋ ረድኤት ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ በነፍሱ ላይ የመለወጥ ኃይሉን ማሳየቱ የማይቀር ነው። በእርሱ የኃይልና የጥበብ ምንጭ በሆነው ፈቃድ ፡ የአምላክ ግልጸት ምሥጢራት በዚህ ሁኔታ ታውጀዋል።*

*“የአምላክን ጥቅሶች በየዕለቱ ጧትና ማታ ድገሙ። የማይደግማቸው ማንም ሰው በእርግጥ ለአምላክ ቃል-ኪዳንና ለእርሱ አዲሱ ሥርዓት የገባውን ቃል ሳያሟላ ቀርቷል፡ ከእነዚህ ቅዱሳት ጥቅሶች ፊቱን የሚያዞር ማንም ሰው ደግሞ በእርግጥ ለማስታወስ ከማይቻል ጊዜ ጀምሮ ከአምላክ ፊቱን አዙሯል። አገልጋዮቼ ሆይ! እያንዳንዳችሁና ሁላችሁ እግዚአብሔርን ፍሩ!”*

## ሀ)ልዩ ልዩ ጸሎቶች

የማለዳ ጸሎት::

1

በጾም ወይም በሌሎች የማለዳ ጊዜያት የሚደረግ::

አምላኬ ጌታዬ ሆይ! እኔ አገልጋይህ የአገልጋይህም ልጅ ነኝ:: የአንድነትህ የቀኑ ኮከብ ከፈቃድህ ጎሕ ባበራበትና በትእዛዝህ መጻሕፍት ውስጥ በተደነገገው መሠረት ጮራውን በመላው ዓለም ላይ በፈነጠቀበት በዚህ ማለዳ ከመደቤ ነቅቻለሁ::

አምላኬ ሆይ፡ ወደ ዕውቀትህ ብርሃን ውበት ለመንቃት በመቻላችን ለአንተ ምስጋና ይድረስህ:: ጌታዬ ሆይ፡ አንተን በስተቀር ሌላውን ሁሉ ለመተው የሚያስችለንንና ከአንተ በስተቀር ከማንኛውም ቁራኛነት የሚያነጻንን ላክልን:: በተጨማሪም ለእኔ፡ ለእኔ ውድ ለሆኑትና ለዘመዶቼ፥ ለወንዱም ለሴቱም፡ የዚህኛውንና የመጪውን ዓለም መልካም ነገር ሁሉ እዘዝልን:: አቤቱ፡ አንተ የመላው ፍጥረት ተወዳጅና የጠቅላላው ሁለንተን ዓለም ምኞት የሆንክ ሆይ፡ የእርኩሱ አንሾኳሻኪ መገለጫዎች ከአደረግሃቸው፡ ከእነዚያ በሰዎች ልቦናዎች ከሚያንሾኳሹኩት፡ በማይቋረጠው ጠባቂነትህ ጠብቀን:: አንተ የፈቀድከውን ለማድረግ የማይሳንህ ነህና:: በእውነት፡ አንተ ፍጹም ኃያሉ፡ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፡ በገዛ ራሱም ነዋሪው ነህና::

ጌታ አምላኬ ሆይ፡ እርሱን ከሁሉም በላቁት ስለሚዎችህ ላይ የሰየምከውን፡ በእርሱም ጻድቃንን ከኃጢአን የለየህበትን ባርከው፡ እኛም አንተ የምትፈቅደውንና የምትወደውን እንድንሠራ በጸጋህ እርዳን። በተጨማሪም፡ አምላኬ ሆይ፡ የአንተ ቃላትና ፊደላት የሆኑትን፡ ፊታቸውን ወደአንተ ያቀኑትን፡ ወደአንተም ገጽታ የዞሩትን፡ ጥሪህንም ያዳመጡትን ሁሉ ባርካቸው።

በእውነቱ አንተ የሰዎች ሁሉ ጌታና ንጉሥ፡ በሁሉም ነገሮች ላይ የበላይ ነህ።

## የጥዋት ጸሎት።

2

አምላኬ ሆይ፡ በአንተ ጥላ ሥር ነቅቻለሁ፡ ይህንንም ጥላ የሚሻ ሁሉ በጥበቃህ ክልልና በተከላካይነትህ ምሽግ ውስጥ መኖር ይገባዋል። ጌታዬ ሆይ፡ ውጫዊ ሰውነቴን በልግስናህ የጧት ብርሃን እንዳበራኸው ሁሉ፡ ውስጣዊ ሕልውናዬንም በግልጸትህ ጎሕ ደማቅ ብርሃን አብራው።

3

አምላኬ ሆይ፡ ዛሬ ጧት በአንተ ጸጋ ከእንቅልፌ ተነሥቻለሁ፡ ሙሉ በሙሉ በአንተ በመተማመንና ራሴን ለአንተ ጥበቃ በመስጠት ከቤቴ ወጥቻለሁ። ከምሕረትህ መንግሥተ ሰማይ፡ ከአጠገብህ በረከ ላክልኝ፡ ልክ ሃሳቤን በትኩረት በአንተ ላይ በማድረግ



በጥበቃህ ሥር ሆኜ ከቤቴ ለመውጣት እንዳስቻልከኝ ሁሉ፡ በደህና ወደ ቤቴ መልሰኝ። ከአንተ ከአንዱ፡ ወደር ከሌለው ፡ ከሁሉን አዋቂው፡ ከፍጹም ጠቢቡ በስተቀር ሌላ አምላክ የለምና።

## የማታ።

4

አምላኬ፡ ጌታዬ፡ የልቤ ዓላማ ሆይ! ይህ አገልጋይህ፡ እንክብካቤህንና ጥበቃህን በመማጸን በምሕረትህ ጥላ ሥር ሊተኛ፡ በጸጋህም ከለላ ሥር ሊያርፍ ይፈልጋል።

ጌታዬ ሆይ፡ አንተን ብቻ እንጂ ሌላውን ነገር ሁሉ እንዳያዩ ዓይኖቼን እንቅልፍ ከቶ በማያታልለው ዓይንህ እንድትጠብቅልኝ እለምንሃለሁ። ዓይኖቼ ያንተን ምልክቶች ለማየትና የግልጸትህን አድማስ ለመመልከት እንዲችሉ የማየት ኃይላቸውን አበርታ። አንተ በእርሱ ሁሉን ቻይነት መገለጽ ፊት የሥልጣን ሕልውና የተንቀጠቀጠለት ነህና።

ከአንተ ከፍጹም ኃያሉ፡ ከሁሉን አስገባሪው፡ ከማይገታው በቀር ሌላ አምላክ የለም።

5

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፡ አንተን የሚናፍቁት ከአንተ በመለየታቸው ምክንያት ዓይኖቻቸው ሳያንቀላፉ እኔ እንዴት መተኛትን መምረጥ እችላለሁ፤ የተወዳጆችህም ነፍሶች ከአጠገብህ በጣም በመራቃቸው ክፉኛ አዝነው እያሉ እንዴት ለማረፍ እጋደማለሁ?

ጌታዬ ሆይ፡ መንፈሴንና መላውን ሕያውነቴን ለቀኙ እጅህ ኃይልና ጥበቃ አደራ ሰጥቻለሁ፡፡ እራሴን በአንተ ኃይል ትራሴ ላይ አሳርፋለሁ፤ በአንተ ፍላጎትና መልካም ፈቃድ አቀናዋለሁ፡፡ በእውነቱ አንተ አኑዋሪው፡ ጠባቂው፡ ፍጹም ኃያሉና፡ ከሁሉም በላይ ኃይል የተመላው ነህ፡፡

በኃያልነትህ! ተኛቼም ሆነ ነቅቼ አንተ ከምትፈልገው በስተቀር ሌላ አልጠይቅም፡፡ እኔ አገልጋይህና በመዳፎችህ ውስጥ ያለሁ ነኝ፡፡ የመልካም ፈቃድህን መዓዛ ለማወድ የሚችል ተግባር ለመፈጸም እንድችል በጸጋህ እርዳኝ፡፡ በእውነቱ የእኔና የእነዚያ ወደ አንተ የመቅረቡ ዕድል የተሰጣቸው ምኞት ይህ ነውና፡፡ የዓለማት ጌታ ሆይ፡ ምስጋና ለአንተ ይሁን!

6

አንተ እውነትን ፈላጊ ሆይ! እግዚአብሔር ዓይንህን እንዲከፍትልህ ከፈለግህ፡ በእኩለ ሌሊት እግዚአብሔርን መማጸን፡ እንዲህ በማለት ወደ እርሱ መጸለይና ከእርሱ ጋር መቋረብ አለብህ፡

ጌታ ሆይ፡ ፊቴን ወደ አንድነትህ መንግሥት በመመለስ በምሕረትህ ባሕር ውስጥ ሰጥሜአለሁ፡፡ ጌታ ሆይ፡ በዚህ ጨለማ ሌሊት እይታዬ የአንተን ብርሃኖች በማየት እንዲበራ አድርግልኝ ፡ በዚህም ድንቅ ዘመን በፍቅርህ ወይን ጠጅ አስደስተኝ፡፡ ጌታ ሆይ ፡ የክብርህን ብርሃን እንዳይና ወደ ውበትህ እንድሳብ ፡ ጥሪህን እንድሰማ አድርገኝ፡ የመንግሥተ ሰማይህንም በሮች በፊት ለፊቴ ክፈትልኝ፡፡

በእውነቱ፡ አንተ ሰጪው፡ ለጋሱ፡ መሐሪው፡ ይቅር ባዩ ነህና፡፡



## የባሃኢ ጋብቻ

7

በባሃኢ መንፈሳዊ ጉባኤ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖራቸው በሚችል ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ምሥክሮች ፊት፡ በሙሽራይቱና በሙሽራው ተራ በተራ የሚደገመው፡ በኪታበ አቅዳስ (ከሁሉ በላይ ቅዱስ መጽሐፍ) ውስጥ የተደነገገው የባሃኢ የጋብቻ ቃል ኪዳን ጥቅስ ከዚህ የሚከተለው ነው፡

*"በእውነቱ፡ እኛ ሁላችንም በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት እንኖራለን"*

## የጋብቻ ጸሎት

8

እርሱ ለጋሱ፡ ጸጋ የተመላው ነው!

በእውነቱ እርሱ አንዱ፡ አንድዬው፡ የማይገኘው፡ የተከበረው፡ መሆኑን በገዛ ራሱ ሕያውነት ለመሠከረው፡ ለጥንታዊው፡ ለዘላለም ነዋሪው፡ ለማይለወጠው፡ ለዘላለማዊው አምላክ ምስጋና ይሁን! በእውነቱ የእርሱን አንድነት

በማረጋገጥ፡ የእርሱን አንድዬነት በመቀበል፡ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እንመሰክራለን። እርሱ፡ ከእርሱ ከራሱ በስተቀር ከሌላ ከማንም ሰው የእርሱን ስም ማንጣት የነጻ፡ ከራሱ በስተቀር ከሌላ ከማንም ገለጻ ነፃ ሆኖ፡ ወደ አቅራቢያቸው ለመድረስ በማይቻሉ ከፍታዎች ፡ በላቀ ደረጃው የላቁ ከፍታዎች ላይ ለዘለዓለም ኖሮአል።

እርሱ ጸጋንና በጎ ፈቃድን ለሰዎች ለመግለጽ፡ ዓለምንም ሥርዓት ለማስያዝ ስለፈለገ ፡ ትእዛዛትን ገለጸ፡ ሕግጋትንም ደነገገ፡ በእነዚህም ሕግጋት መካከል የጋብቻን ሕግ መሠረተ፡ የደህንነትና የመዳንም ምሽግ አደረገው፡ ከቅድስና መንግሥተ ሰማይም በተላከው በእርሱ ከሁሉም በላይ ቅዱስ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ እንድናከብረው አዘዘን። የእርሱ ክብር ታላቅ ነው! እንዲህ ይላል፡- *'ሰዎች ሆይ፡ በአገልጋዮቼ መካከል እኔን የሚያስታውስ ከእናንተ_ይገኝ ዘንድ ተጋቡ፡ ይህ ለእናንተ ከትእዛዞቼ መካከል አንዱ ነው፡ ለእናንተ ለራሳችሁ እንዲረዳችሁ ታዘዙት።'*

.9

አምላኬ ሆይ፡ ክብር ለአንተ ይሁን! በእውነቱ ይህ አገልጋይህና ይህች አገልጋይህ በምሕረትህ ጥላ ሥር ተሰባስበው፡ በአንተ ደግነትና ቸርነት በጋብቻ ተጣምረዋል። ጌታ ሆይ! በዚህ ዓለምህና በመንግሥትህ ውስጥ እርዳቸው፡ በቸርነትህና በጸጋህ እያንዳንዱን መልካም ነገር አድላቸው። ጌታ ሆይ! ለአንተ በአገልጋይነታቸው ተግባር ላይ አበርታቸው ፡ ለአንተ



እንዲያገለግሉ፡ በዓለምህም የስምህ ምልክቶች እንዲሆኑ አድርጋቸው። በዚህ ዓለምና በሚቀጥለውም ዓለም በማያልቁ ችሮታዎችህ ጠብቃቸው። ጌታ ሆይ! የመሐሪነትህን መንግሥት እየተማጸኑ፡ የአንድነትህንም ዓለም እርዳታ እየጠየቁ ናቸው። በእውነቱ የአንተን ትእዛዝ በማክበር ተጋብተዋል። እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ የስምምነትና የአንድነት ምልክቶች እንዲሆኑ አድርጋቸው። በእውነቱ ፡ አንተ ምንም የማይሳነው ፡ በሁሉ ሥፍራ የሚገኘውና ፍጹም ኃያሉ ነህና።

<u>የፈውስ</u>።

10

አምላኬ ሆይ፡ ስምህ መፈወሻዬ ነው፡ አንተንም ማስታወስ መድኃኒቴ ነው። ወደ አንተ መቅረብ ተስፋዬ ነው ፡ ለአንተም ያለኝ ፍቅር ባልደረባዬ ነው። የአንተ ምሕረት በዚህና በሚቀጥለው ዓለም መፈወሻዬና እርዳተዬ ነው። በእውነቱ፡ አንተ ፍጹም ለጋሱ፡ ሁሉን አዋቂው ፡ ፍጹም ጠቢቡ ነህና።

11

በፈዋሹ፡ በአርኪው ፡ በረዳቱ፡ በእግዚአብሔር ስም! አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይሁን!

አምላኬና ተወዳጄ ሆይ! አቤቱ አንተ የመጨረሻ ዕድል መንግሥትና ተፈጻሚ የማድረግ ሥልጣን በመዳፍህ ውስጥ ያለው ሆይ፡ በዚህ ሕመመተኛ ላይ

ከእያንዳንዱ በሽታ፡ ድከመትና ፈተና የሚያነጻውን ከምሕረትህ ደመናዎች እንድታዘንብበት፡ በመፈወሻህም ውቅያኖስ ውስጥ እንድታሰጥመው፡ ምሕረትህ ሁሉን ነገር በቀደመበት ስምህ፡ ከገጽታህ አድማስ ባበራውና ጸጋህ በእነዚያ በምድርና በሰማይ በሚገኙት ሁሉ ላይ ፍጹም በሆነበት በህቡዕ ስምህ ውበት ፀሐይ እለምንሃለሁ።

በእውነት፡ አንተ የፈቀደውን ሁሉ አድራጊው ነህና፡ በእርግጥም፡ አንተ ይቅር ባዩና አዛኙ ነህና።

12

ጌታ አምላኬ ሆይ፡ ክብር ለአንተ ይሁን! ይህቺን ለመጠጊያ ወደ አንተ የሸሸችውን፡ የእርሱን አንተ ራስህን በእርሱ ላይ የከሰትከውን ተገን የፈለገችውን፡ መላ እምነቷንና ተስፋዋንም በአንተ ላይ የጣለችውን ሴት አገልጋይ እንድትጠብቅ - እርሱ የአንተ ውበት የሆነው በእምነትህ ዙፋን ላይ በተሰየመበት ስምህ፡ አንተም ሁሉንም ነገሮች በምትለውጥበት፡ ሁሉንም ነገሮች አንድ ላይ በምትሰበስብበት፡ ሁሉንም ነገሮች ስለሥራቸው ልትጠይቃቸው በምትጠራበት፡ ለሁሉም ነገሮች ወሮታቸውን በምትሰጥበት፡ ሁሉንም ነገሮች ጠብቀህ በምታቆይበት፡ ሁሉንም ነገሮች በሕይወት በምታኖርበት ስምህ እለምንሃለሁ።



አምላኬ ሆይ፡ እርሷ ታማ በመፈወሻህ ዛፍ ጥላ ሥር ገብታለች፡ ተሰቃይታ ወደ ጥበቃህ ከተማ ሸሽታለች፡ በሽተኛ ሆና የችሮታህን ምንጭ መነሻ ፈልጋለች ፡ ከፉኛ ተበሳጭታ ወደ ማረጋጋትህ ምንጭ ለመድረስ በፍጥነት ገስግሳለች፡ በኃጢአት ሸክም ተጨንቃ ፊቷን ወደ ይቅር ባይነትህ መንበር መልሳለች።

አምላኬና ተወዳጄ ሆይ፡ በሥልጣንህና በፍትራዊ ደግነትህ ፡ በአዳኝ ቅባትህና በመፈወሻህ ልብስ አልብሳት፡ ከምሕረትህና ከችሮታህ ጽዋ እስክትረካ እንድትጠጣ አድርጋት። በተጨማሪም፡ ከእያንዳንዱ መከራና ሕመም፡ ከሁሉም ስቃይና በሽታ፡ ለአንተ ከሚያስጠይፈው ከማንኛውም ነገር ጠብቃት።

አንተ በእውነት፡ ከአንተ ከራስህ በስተቀር ከሌላው ሁሉ በላይ በጣም የላቅህና የተከበርክ ነህ። በእውነት፡ አንተ ፈዋሹ፡ ፍጹም አርኪው፡ ጠብቆ አኑዋሪው፡ ዘላለም ይቅር ባዩ፡ ከሁሉ በላይ መሐሪው ነህና።

13

አምላኬ ሆይ፡ አንተ በስሞቹ ሕመምተኞች የሚፈወሱት፡ በሽተኞችም የሚድኑት፡ የተጠሙትም የሚረኩት፡ ከፉኛ የተበሳጩትም የሚረጋጉት፡ መንገድ የሳቱትም የሚመሩት፡ የተዋረዱትም የሚከበሩት፡ ድሆችም የሚበለጽጉት፡ አላዋቂዎችም ዕውቀት የሚያገኙት፡ የተከዙትም የሚደሰቱት፡

ኃዘንተኞችም የሚጽናኑት: የቀዘቀዙትም የሚሞቁት: የተረገጡትም ከፍ የሚደረጉት ነህ:: አምላኬ ሆይ: በስምህ አማካይነት የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ተቀሰቀሱ: ሰማያትም ተዘረጉ: ምድርም ተመሠረተች: ደመናዎቹም እንዲንሳፈፉና በምድር ላይ እንዲያዘንቡ ተደረጉ:: ይህም በእውነቱ: ለፍጡሮችህ ሁሉ የአንተ ጸጋ ምልክት ነው::

ስለዚህ: በዚህ ሌሊት: በዚህ አንተ በፍጥረትህ መንግሥት ከአንተ ፍጹም ክብር የተመላ ህልውና ጋር በአዛመድኸው ሕፃን ላይ: ከምሕረትህ ደመናዎች የመፈወሻህን ዝናቦች እንድታዘንብበት: አንተ አምላክነትህን በከሰትህበት: እምነትህንም ከፍጥረት ሁሉ በላይ ከፍ በአደረግህበት ስምህ: የአንተ ከሁሉ የላቁ ስያሜዎችና ከሁሉም በላይ የተከበሩ ባሕርያት: የአንተ ከሁሉ የላቀውና ከሁሉም በላይ የተከበረው ሕያውነት በሚወደስባቸው ባሕርያት ሁሉ እማጸንሃለሁ:: አምላኬ ሆይ: በአንተ ጸጋ: በደህንነትና በጤና ልብስ አልብሰው : አቤቱ አንተ ተወዳጁ ሆይ: ከእያንዳንዱም ስቃይና ሕመም: ለአንተም ከሚያስጠላው ከማንኛውም ነገር ጠብቀው:: በእውነቱ:የአንተ ኃያልነት ለሁሉም ነገሮች ብቁ ነው:: በእውነቱ: አንተ ከሁሉም በላይ ኃይል የተመላው: በገዛ ራሱም ነዋሪው ነህ:: ከዚህም በላይ: አምላኬ ሆይ: የዚህንና የሚቀጥለውን ዓለም መልካም ነገሮች: የቀድሞዎችንም የኋለኞችንም ትውልዶች መልካም ነገሮች ሁሉ ላክለት:: በእውነቱ: የአንተ ኃያልነትና የአንተ ጥበብ ለዚህ ሁሉ ብቁ ናቸውና::



14

ጌታ አምላኬ ሆይ: ክብር ለአንተ ይሁን!

ተማጽኜሃለሁ እርሱን: አንተን በጽናት በመያዝ : ወደ አንተ የተመለሰውን: በምሕረትህም ላይ የተንጠላጠለውን: የፍቅራዊ መለኮታዊ ጥበቃህንም ዘርፍ አጥብቆ የያዘውን ከማንኛውም አደጋ እንድትጠብቀው: በእርሱ አማካይነት የአንተን መርሖ ዓርማዎች ከፍ በአደረግህበት: የፍቅራዊ ደግነትህንም ብርሃን በአበራህበት: የጌታነትህንም ሥልጣን በገለጽህበት: የስሞችህም ፋኖስ በባሕርያትህ መቅረዝ ላይ በተከሰተበት: እርሱም የአንድነትህ መቅደስና የመላቀቅ ክስተት የሆነው በአበራበት: የአንተ መርሖ ጎዳናዎችም በታወቁበት: የበጎ ፈቃድህም መንገዶች በተቀየሱበት: የስሕተት መሠረቶች እንዲንቀጠቀጡ: የክፋት ምልክቶችም እንዲጠፉ በተደረጉበት: የጥበብ ምንጮችም በፈለቁበት: መንግሥተ ሰማያዊውም ገበታ ከላይ በተላከበት: አገልጋዮችህንም ጠብቀህ በአኖርክበትና ፈውስህንም በለገስክበት: ለአገልጋዮችህ ርኅራኄ የተመላበት ምሕረትህን በአሳየህበትና በፍጡራንህም መካከል ይቅር ባይነትህን በገለጽክበት ስምህ እማጸንሃለሁ:: እንግዲህ ፈውስህን ላክለት: የተሟላም አድርገው: በአንተ የተለገሰ ጽናት : በከፍተኛነትህም የተበረከተ መረጋጋት አጎናጽፈው::

በእውነቱ: አንተ ፈዋሹ: አኑዋሪው: ረዳቱ: ፍጹም ኃያሉ: ኃይል የተመላው: ንዑዱ: ሁሉን አዋቂው ነህና::

15

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! በበረከትህ ውሀዎች አማካይነት ከእያንዳንዱ ስቃይና የጤና መቃወስ፡ ከማናቸውም ድክመትና አቅመ ቢስነት ሁሉ እንድታነጻኝ፡ በመፈወሻህ ውቅያኖስም፡ በጸጋህ የቀኑ ኮከብ ብርሃን ውበትም፡ አገልጋዮችህን በአስገበርክበት ስምህም፡ ከሁሉ በላይ በተከበረው ቃልህ ሁሉን የሚናኝ ኃይልም፡ ከሁሉ በላይ ግርማ በተመላው ብዕርህ ሁሉን ቻይነትም፡ በሰማይና በምድር ከሚገኙት ሁሉ መፈጠር በቀደመው ምሕረትህም እለምንሃለሁ።

ጌታዬ ሆይ፡ ተማጽኝህ በበረከትህ በር ላይ ሲጠባበቅ፡ እርሱ ተስፋውን በአንተ ላይ ያደረገውም በቸርነትህ ገመድ ላይ ተንጠላጥሎ ታየዋለህ። እርሱ ከጸጋህ ውቅያኖስና ከፍቅራዊ ደግነትህ የቀኑ ኮከብ የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንዳትነፍገው እማጸንሃለሁ።

አንተ የሚያስደስትህን ለማድረግ ኃይል አለህ ። ከአንተ፡ ከምንጊዜም ይቅር ባዩ፡ ከፍጹም ቸሩ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

ለስብሰባ

16

ጌታ አምላኬ ሆይ፡ አንተ የተከበርክ ነህ! ለእኔና የአንተን ገጽ ለማየት ለፈለጉት ሁሉ ከቸርነትህና በረከት ከተመላበት ጸጋህ መስጠቱ የሚጠበቀውን፡ ከስጦታዎችህና ከችሮታዎችህ መለገሱም ተገቢ የሆነውን እንድትልክልን፡ በኃይል በሚነፍሱት የጸጋህ



ነፋሶች፥ በእነዚያም በዓላማህ ንጋቶችና በመንፈሳዊ የእውቀት ብልጭታህ የንጋት ሥፍራዎች በሆኑት እማጸንሃለሁ። ጌታዬ ሆይ፥ እኔ ምስኪንና ጉስቁል ነኝ! በሀብትህ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥመኝ፤ የተጠማሁ ነኝ፥ ከፍቅራዊ ደግነትህ የሕይወት ውሀዎች እንድጠጣ አድርገኝ።

አገልጋዮችህን ጸጋ በተመላበት አምላካዊ ጥበቃህ ዛፍ ጥላ ሥር በአንድ ላይ እንድትሰበስባቸው፥ በአንተው በራስህና በእርሱ የአንተ የራስህ ህልውና ክስተትና በሰማይና በምድር ለሚገኙት ሁሉ ክፉውን ከበጎ የሚለይ ቃልህ አድርገህ በሰየምከው እማጸንሃለሁ። ከፍሬዎቹ እንዲሳተፉ፥ ወደቅጠሎቹ መንኮሻኮሽ፥ ከቅርንጫፎቹ ላይ ወደሚያዜመውም ወፍ ድምጽ ጣፋጭነት ጆሮዎቻቸውን እንዲያቀኑ እርዳቸው። በእውነቱ፥ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፥ የማይደረስበቱ፥ ፍጹም ኃያሉ፥ ከሁሉም በላይ ጸጋ የተመላው ነህና።

17

አቤቱ፡ አንተ መሐሪው አምላክ ሆይ! አቤቱ፡ አንተ ኃያልና ኃይል የተመላው ሆይ! አቤቱ፡ አንተ ከሁሉም በላይ ሊጋስ አባት ሆይ! እነዚህ አገልጋዮች ወደ አንተ ተመልሰው በአንተ ደጅሰላም ለመማጸን፥ ከአንተ ታላቅ መተማመኛ የአንተን የማያልቁ በረከቶች ለመለመን በአንድ ላይ ተሰባስበዋል። እነርሱ ከአንተ መልካም ደስታ በስተቀር ሌላ ዓላማ የላቸውም። የሰውን ዘር ዓለም ከማገልገል በስተቀር ሌላ ዕቅድ የላቸውም።

አምላክ ሆይ! ይህን ስብሰባ ብሩህ አድርገው። ልቦችን መሐሪዎች አድርጋቸው። የቅዱስ መንፈስን በረከቶች አውርድላቸው። የመንግሥተ ሰማይ ኃይል አጎናጽፋቸው። የመንግሥተ ሰማይ አዕምሮዎች በመስጠት ባርካቸው። በሙሉ ትሕትናና ፀፀት በተመላበት ልብ ወደ አንተ መንግሥት በመመለስና፡ ለሰው ዘር ዓለም አገልግሎት በመስጠት ሥራ እንዲጠመዱ ቅንነታቸውን አብዛ። እያንዳንዱ ብሩህ ሻማ ይሁን። እያንዳንዱ አንጸባራቂ ኮከብ ይሁን። እያንዳንዱ በአምላክ መንግሥት ውስጥ ውበት የተመላ ቀለምና አስደሳች መዓዛ ያለው ይሁን።

አቤቱ አንተ ለጋስ አባት ሆይ! ቡራኬዎችህን አጎናጽፈን ። ጉድለቶቻችንን አትመልከት። በጥበቃህ መጠለያ ሥር ጠልለን። ኃጢአቶቻችንን አትመልከት። በምሕረትህ ፈውሰን። እኛ ደካሞች ነን፡ አንተ ግን ኃያል ነህ። እኛ ምስኪኖች ነን፡ አንተ ግን ሀብታም ነህ። እኛ ሕሙማን ነን፡ አንተ ደግሞ ሐኪም ነህ። እኛ ችግረኞች ነን፡ አንተ ግን ከሁሉ በላይ ቸር ነህ።

አምላክ ሆይ! ሀብትህን አጎናጽፈን። አንተ ኃይል የተመላው ነህ። አንተ ሰጪው ነህ። አንተ ለጋሱ ነህ።





18

ፍጹም ኃይል የተመላው በጸሎት የላቀ ድል ለማግኘት እንድትችሉ ይረዳችሁ ዘንድ፡ ወደ መንፈሳዊ ጉባኤው ክፍል በምትገቡበት ጊዜ፡ በእግዚአብሔር ፍቅር በሚርገበገብ ልብና እርስትን ከማስታመስ በቀር ከሌላ ነገር ሁሉ በንጻ አንደበት ይህን ጸሎት አድርጉ።

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! እኛ በዚህ ታላቅ ቀን ከአንተ በቀር ከሁሉም ተላቅቀን ወደ ቅዱስ ገጽህ በፍቅር የተመለስን አገልጋዮችህ ነን። በሰው ዘር መካከል ቃልህን ከፍ ለማድረግ ባለን የዓላማ ስምምነት በአመለካከታችንና በአስተሳሰባችን ተዋሕደን በዚህ መንፈሳዊ ጉባኤ ተሰብስበናል። ጌታ አምላካችን ሆይ! የአንተ መለኮታዊ መርሖ ምልክቶች፡ በሰዎችም መካከል የላቀው እምነትህ ሰንደቅ ዓላማዎች፡ ለኃያሉ ቃል ኪዳንህም አገልጋዮች እንድንሆን፡ አንተ ከሁሉም የላቅህ ጌታችን ሆይ፡ በአብሀ መንግሥትህ የመለኮታዊ አንድነትህ መገለጫዎች ፡ በሁሉም አካባቢዎች ላይ የሚያበሩ አንጸባራቂ ከዋክብትም አድርገን። ጌታ ሆይ! በአስገራሚው ጸጋህ ሞገድ የሚንቀሳቀሱ ባሕሮች፡ ፍጹም ክብር ከተመሉት ከፍታዎችህ የሚጎርፉ ጅረቶች፡ በመንግሥተ ሰማያዊው እምነትህ ዛፍ ላይ ያሉ መልካም ፍሬዎችና በመለኮታዊ የወይን እርሻህ ውስጥ በጸጋህ ልዝብ ነፋሶች የሚወዛወዙ ዛፎች እንድንሆን እርዳን። አምላክ ሆይ! አስተሳሰቦቻችን፡ አመለካከቶቻችንና ስሜቶቻችን ልክ እንደ አንድ እውነት በመላው ዓለም የአንድነት መንፈስ ይገልጹ ዘንድ ፡ ልክ እንደ አንድ ባሕር ሰንበሮች አንድ

እንድንሆንና እንደ አንጸባራቂው ብርሃንህ ጨረሮች በአንድነት እንድንጣመር፥ ነፍሶቻችን ለመለኮታዊ አንድነትህ ጥቅሶች እንዲገዙ ፡ ልቦቻችንም በጸጋህ ጎርፎች እንዲደሰቱ፡ አድርጋቸው፡፡ አንተ ጸጋ የተመላው፡ ለጋሱ፥ ሰጪው፥ ፍጹም ኃያሉ ፡ መሐሪው፥ ሩኅሩኁ ነህና፡፡

19

አቤቱ፡ አንተ ሩኅሩኁ አምላክ ሆይ! በዚህ መንፈሳዊ ጉባኤ በታላቅ ትሕትና በአንድ ላይ ተሰባስበናል፡፡ አንድ እንድንሆንና እንድንስማማ፥ እርስ በርሳችንም እንደማርና ወተት በጣፈጠ ግንኙነት እንድንቀራረብ፡ ለሰውም ዘር አንድነት መንግሥት ምጽዓት ምክንያት እንድንሆን ፊቶቻችንን ወደ አንተ መንግሥት በመመለስ ማረጋገጫህንና እርዳታህን እንለምናለን፡፡ ምኞታችን እንዲፈጸምልን በንጹህ ልብና በብሩህ መንፈስ ወደ አንተ እንድንጸልይና እንድንለምንህ እርዳን፡፡

ፍጹም ኃያሉ ሆይ! በጸጋህና በቸርነትህ ተመልከተን እንጂ ኃጢአታችንን አትመልከት፡፡ ጉድለቶቻችንን ይቅር በለን፡፡ በረከትህን አውርድልን፡፡ የፍቅርህን እሳት አቀጣጥለህ የአጉል አምልኮን፡ የስሜትንና የምኞትን ግርዶሽ አቃጥለህ አጥፋቸው፡፡ ከእኔነት ድክመት ተከላክለህ ጠብቀን፡ በመሐሪነትህ ዛፍ ጥላ ሥር ከልለን፡ የመንፈስንም ፀጥታና ዕረፍት ስጠን፡፡

በእውነት፡ አንተ ኃይል የተመላው ፡ ኃያሉ ነህና፡፡



20

በመንፈሳዊ ጉባኤ ስብሰባ መዝጊያ ላይ የሚደረግ ጸሎት

አምላክ ሆይ! አምላክ ሆይ! እኛ በአንተ አምነን፡ በምልክቶች ላይ ባለን እምነት እርግጠኞች፡በቃል ኪዳንህና በአዲሱ ሥርዓትህ ጸንተን፡ ወደ አንተ ተስበን፡ በፍቅርህ እሳት ተቀጣጥለን፡ የእምነትህም ቅን አማኞች ሆነን በዚህ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ተሰባስበን መገናኘታችንን ከማይታየው የአንድነትህ መንግሥት ተመልከተን፡፡ እኛ በአንተ የወይን እርሻ ውስጥ በማገልገል ላይ የምንገኝ፡ ሃይማኖትህን አስፋፊዎች ፡ ራሳችንን ለአንተ አገልግሎት የሰጠን የአንተ ገጽታ አምላኪዎች፡ ለተወዳጆችህ ትሑታን፡ በበርህም ፊት ታዛዦች የሆንን፡ ሕጉያንህን በማገልገል ተግባራችንም ተቀባይነት ማግኘታችንን እንድታረጋግጥልን፡ በማይታዩት ሠራዊቶችህም እንድትደግፈን፡ ለአንተ ለምናበረክተውም አገልግሎት ሽንጦቻችንን እንድታጠናክርልን፡ ለትእዛዝህ ትሑታን ተገዢዎችና ከአንተም ጋር የምንቀረብ አምላኪ አገልጋዮች እንድታደርገን አንተን በመማጸን ላይ የምንገኝ አገልጋዮችህ ነን፡፡

አቤቱ፡ አንተ ጌታችን ሆይ! እኛ ደካሞች ነን፡ አንተ ደግሞ ኃያሉ፡ ኃይል የተመላው ነህ፡፡ እኛ ሕይወት አልባዎች ነን፡ አንተ ደግሞ ታላቁ ሕይወት ሰጪ መንፈስ ነህ፡፡ እኛ ችግረኞች ነን፡ አንተ ደግሞ በሕይወት አኗሪው፡ ኃይል የተመላው ነህ፡፡

አቤቱ፡ አንተ ጌታችን ሆይ! ፊቶቻችንን ምሕረት ወደተመላው ገጽታህ መልስልን፡ ከመንግሥተ-ሰማያዊው የአንተ ገበታ የተትረፈረፈውን የአንተን ጸጋ መግበን፡ በላቂት የአንተ መላእክት ሠራዊት እርዳን፡ በአብሃ መንግሥትም ቅዱሳን አማካይነት አጠንክረን ::

በእውነቱ፡ አንተ ቸሩ፡ መሐሪው ነህ:: አንተ የታላቅ በረከት ባለቤት ነህ፡ በእርግጥም አንተ ሩኅሩኁና ጸጋ-የተመላው ነህና::

<u>ለሕፃናት</u>

21

ጌታ አምላኬ ሆይ፡ ምስጋና ለአንተ ይሁን! ይህ ሕፃን በጸጋህ የፍቅራዊ ምሕረትህንና ርኅራኄ የተመላበት የአምላካዊ ጥበቃህን ጡት እንዲጠባ፡ የመንግሥተ ሰማያዊ ዛፎችህንም ፍሬዎች እንዲመገብ ፈቃድህ ይሁን:: አንተ ራስህ በላቀው ፈቃድህና ሥልጣንህ ኃይል ስለፈጠርከውና ወደ መኖር ስለጠራኸው ፡ ለአንተ እንጂ ለሌላ ለማንም እንክብካቤ እንዲተው አታድርገው:: ከአንተ ከፍጹም ኃያሉ፡ ከሁሉን-አዋቂው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም::

አቤቱ፡ አንተ ከሁሉም በላይ ተወዳጁ ሆይ፡ የተወደስክ ነህ፡ ከሁሉ የላቀ በረከትህን ጣፋጭ ሽታና የቅዱስ ስጦታዎችህን መዓዛዎች በላዩ አርብብበት:: ከዚያም፡አቤቱ፡ አንተ የስሞችና የባሕርያት መንግሥትን በመዳፍህ ውስጥ ይዘህ ያለኸው ሆይ፡



ከሁሉም በላይ በተከበረው ስምህ ጥላ ሥር መጠለያ ለመፈለግ አስችለው:: በእውነቱ፡ አንተ የፈቀድከውን ለማድረግ የማይሳንህ ነህ ፡ በእርግጥም አንተ ኃያሉ፡ የተከበረው፡ ዘለዓለም ይቅር-ባዩ፡ ጸጋ-የተመላው፡ ለጋሱ፡ መሐሪው ነህና::

22

ጌታ አምላኬ ሆይ! ይህ አንተ በማይሻረው ትእዛዝህ መልእክቶችና በፈቃድህ መጻሕፍት ውስጥ የተከበረ ደረጃ እንዲኖራቸው ከፈቀድህላቸው አገልጋዮችህ መካከል ከአንዱ አብራክ የተገኘ ልጅ ነው::

ይህ ልጅ በአገልጋዮችህ መካከል በሳል ነፍስ እንዲሆን ፈቃድህ ይሆን ዘንድ፡ እያንዳንዱን ሰው ወደ ፍላጎቱ ዓላማ ለመድረስ በአስቻልክበት ስምህ እማጸንሃለሁ፡ በስምህ ኃይል አማካይነት እንዲያበራ አድርገው፡ የአንተን ምስጋና ለመናገር፡ፊቱን ወደ አንተ ለመመለስና ወደ አንተ ለመቅረብ አስችለው:: በእውነቱ፡ ከእምቅድመ ዓለም ጀምሮ እንደፈቀድህ ለማድረግ ኃይል የነበረህ፡ እስከ ዘለዓለምም የፈቀድኸውን ለማድረግ የማይሳንህ ሆነህ የምትኖረው አንተ ነህ:: ከአንተ፡ ከተከበረው ፡ ግርማ ሞገስ ከተመላው፡ ከድል አድራጊው ፡ ከኃያሉ ፡ ከሁሉን አስገዳጅ በቀር ሌላ አምላክ የለም::

23

ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! በለጋነት ዕድሜ ያለሁ ሕፃን ነኝ። ከምሕረትህ ጡት ወተት መግበኝ፡ በፍቅርህ እቅፍ ውስጥ አሥልጥነኝ፡ በአንተ መርሖ ትምሕርት ቤት አስተምረኝ፡ በበረከትህ ጥላ ሥር አጎልምሰኝ። ከጨለማ አውጣኝ፡ ደማቅ ብርሃን አድርገኝ፡ ከደስታ ማጣት አድነኝ፡ የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ አበባ አድርገኝ፡ የደጀሰላምህ አገልጋይ እንድሆን አድርገኝ፡ የጻድቃንንም ዝንባሌና ጠባይ አጎናጽፈኝ ፡ ለሰው ዘር ዓለም የበረከት መንስኤ አድርገኝ ፡ በራሴም ላይ የዘለዓለም ሕይወት አክሊል ድፋልኝ!

በእውነቱ፡ አንተ ኀይል የተመላው፡ ኀያሉ፡ ሁሉን የሚያየው፡ ሰሚው ነህና።

24

አምላኬ ሆይ፡ ምራኝ፡ ጠብቀኝ፡ ብሩህ መብራትና አንጸባራቂ ኮከብ አድርገኝ። አንተ ኀያሉና ኀይል የተመላው ነህና።

25

አምላክ ሆይ! እነዚህን ሕፃናት አስተምራቸው። እነዚህ ሕፃናት የአትክልት ሥፍራህ ተክሎች ፡ የመስክህ አበባዎች፡ የአትክልት ቦታህ ጽጌረዳዎች ናቸው። ዝናብህ እንዲዘንብላቸው፡ የእውነት ፀሐይ ከፍቅርህ ጋር እንዲበራላቸው አድርግ። ይሠለጥኑ፡ ያድጉና ይዳብሩ፡ በከፍተኛ ውበትም ይታዩ ዘንድ፡



የአንተ ልዝብ ነፋስ እንዲያድሳቸው ፈቃድህ ይሁን። አንተ ሰጪው ነህ። አንተ ሩኅሩኅ ነህ።

26

አምላክ ሆይ! ይህን ጨቅላ ሕፃን በፍቅርህ ጉያ ተንከባከበው፡ ከመለኮታዊ ጠባቂነትህም ጡት ወተት ለግሰው። ይህን ለጋ ቡቃያ በፍቅርህ የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ ውስጥ ኮትኩተህ አሳድገው፡ ከጸጋህም በሚወርደው ዝናብ እንዲያድግ እርዳው። የመንግሥተ ሰማይ ልጅ አድርገው፡ ወደ መንግሥተ ሰማያዊው ዓለምህም ምራው። አንተ ኀይል የተመላህና ደግ ነህ፡ አንተ ሰጪው፡ ቸሩ፡ የተትረፈረፈ በረከት ባለቤት ነህና።

ለወጣቶች።

27

ጌታ ሆይ! ይህን ወጣት ብሩህ አድርገው፡ በዚህ ምስኪን ፍጡር ላይ በረከትህን አውርድ፡ ዕውቀትን ለግሰው፡ በየዕለቱም ጥዋት ተጨማሪ ጉልበት ስጠው። ከስሕተት ነፃ ይሆን ዘንድ፡ ለእምነትህ አገልግሎት ራሱን ይሰጥ ዘንድ፡ የተሳሳቱትን እንዲመልስ፡ ዕድለ ቢሶቹንም እንዲመራ፡ ምርኮኞቹን ነፃ እንዲያወጣ፡ ግደለሾቹንም እንዲያነቃቃና ሁሉም አንተን በማስታወስና በማወደስ ይባረኩ ዘንድ በጥበቃህ መጠለያ ውስጥ ጠብቀው። አንተ ኀያሉና በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው ነህና።

28

አቤቱ፡ አንተ ሩኅሩኅ ጌታ ሆይ! ለዚህች የመንግሥተ ሰማይ ልጅ መለኮታዊ ማረጋገጫን ለግሳት፡ በእምነትህ ጠንክራና ጽኑ ሆና ትኖር ዘንድ፡ ልክ በምሥጢራት የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ እንደምትገኝም ዘማሪ ወፍ ፡ በአብሃ መንግሥት በእጅግ በጣም ድንቅ ድምጽ ዜማዎችን ታዜም ዘንድ፡ በዚህም ለእያንዳንዱ ሰው ደስታን ታመጣ ዘንድ፡ በጸጋህ እርዳት። በመንግሥተ ሰማይ ሴት ልጆች መካከል ክፍ አድርጋት፡ ለዘለዓለማዊው ሕይወትም አብቃት።

አንተ ለጋስ፡ ሁሉን አፍቃሪው ነህና።

29

አቤቱ፡ አንተ ከሁሉም በላይ ክብር የተመላህ ጌታ ሆይ! ይህቺን የአንተን ትንሽ ሴት አገልጋይ ብሩክና ደስተኛ አድርጋት፡ በታላቅ ደስታና በከፍተኛ ሐሴት የተመላች በመሆን ጣፋጭ ሽታ ያለው መዓዛ ታሰራጭ ዘንድ፡ በአንድነትህ ደጀሰላም የተወደደች እንድትሆንና ከፍቅርህ ጽዋ እስትረካ እንድትጠጣ አድርጋት። አንተ ኃያሉና ኃይል የተመላው ነህና፡ አንተ ሁሉን አዋቂው፡ ሁሉን የሚያየው ነህና።



30

ጌታ ሆይ! ይህቺን የእግዚአብሔር መንግሥት ልጅ በሁለቱም ዓለማት የተከበረች እንድትሆን እርዳት፡ ከዚህ ከጠፊ የትቢያ ዓለምና ልቦቻቸውን በዚያ ላይ ከአሳረፉት ፊቷን እንድታዞር አድርጋት፡ ከሞት አልባ ዓለም ጋር ግንኙነትና ጥብቅ ትስስር ያላት ለመሆን አስችላት። አንተን ለማገልገል ትነሣ ዘንድ መንግሥተ ሰማያዊ ኃይል ስጣት፡ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋሶችም አጠንክራት።

አንተ ኃያሉ ነህ።

## የባሃኢ መዋጮ።

*"የእግዚአብሔር ወዳጆች ሁሉ ፡ የሚሰጡት ምንም ያህል ትንሽ ቢሆንም እንኳ ፡ የሚችሉትን ያህል ማዋጣት አለባቸው። እግዚአብሔር ማንኛዋንም ነፍስ ከአቅሟ በላይ አይፈልግባትም። እንዲህ ያለው መዋጮ ከሁሉም ማዕከሉችና ከሁሉም ምዕመናን መምጣት አለበት። ...የእግዚአብሔር ወዳጆች ሆይ! ለእነዚህ ለምታዋጡአቸው መዋጮዎች አጸፋ፡ እርሻዎቻችሁ፡ ኢንዱስትሪዎቻችሁና ንግዶቻችሁ በብዙ እጥፍ ጭማሪዎች፡ በመልካም ስጦታዎችና ገጸበረከቶች እንደሚባረኩ እርግጠኞች ሁኑ። አንድ መልካም ሥራ የሚሠራ አሥር እጥፍ ዋጋ ይቀበላል። ለእነዚያ ሀብታቸውን በእርሱ መንገድ ሥራ ላይ ለሚያውሉት፡ ሕያው ጌታ በተትረፈረፈ ሁኔታ ማረጋገጫ እንደሚሰጣቸው ምንም ጥርጥር የለውም።"*

## ለመዋርጮ ጸሎት

31

አቤቱ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! የእውነተኛ አፍቃሪዎችህን ግንባር አብራላቸው፡ የተረጋገጠ ድል በሚያስገኙ መልአካዊ ሠራዊትም ደግፋቸው። የእምነትህን ደህንነት በመጠበቅ፡ እምነታቸውን በአንተ ትዝታ ላይ በማድረግ፡ ልቦቻቸውን ለአንተ ፍቅር በመስጠት፡ ውበትህን በማወደስና አንተን የሚያስደስቱበትን መንገድ በመፈለግ፡ ለሁብታቸው ሳይሳሱ የለገስካቸውን ሁሉ በጎዳናህ በማዋላቸው፡ እግሮቻቸውን በቀጥተኛው መንገድህ ላይ አበርታላቸው፡ ከጥንታዊው ቸርነትህም የቡራኬዎችህን በሮች ክፈትላቸው።

ጌታዬ ሆይ! የተትረፈረፈ ድርሻ፡ የተመደበ ካማና የተረጋገጠ ሽልማት አዘዝላቸው።

በእውነቱ አንተ ደጋፊው፡ ረዳቱ፡ ለጋሹ፡ በረከት የተመላው ፡ ዘለዓለም ሰጪው ነህና።

## ለሙታን።

32

እርሱ አምላክ ነው፡ እርሱ የፍቅራዊ ደግነትና የቸርነት ጌታ የሆነው የተከበረ ነው!

አንተ ምንም የማይሳንህ ጌታ የሆንክ አምላኬ ሆይ፡ ክብር ለአንተ ይሁን። ምንም የማይሳንህ ስለመሆንህና ስለኃያልነትህ ፡ ስለሉዓላዊነትህና ስለፍቅራዊ ደግነትህ፡ ስለጸጋህና ስለሥልጣንህ፡



ስለሕያውነትህ አንድዬነትና ስለህላዌህ አንድነት፡ ከፍጥረት ዓለምና በዚያም ከሚገኙት ሁሉ የተቀደስክና የተከበርክ ስለመሆንህ እመሠክራለሁ።

አምላኬ ሆይ! ከአንተ በቀር ከሁሉም ተላቅቄ አንተን አጥብቄ መያዜንና ወደ ቸርነትህ ውቅያኖስ፡ ወደ ልግሥናህ ሰማይና ወደ ጸጋህ የቀኑ ኮከብ ዞሬ ታየኛለህ።

ጌታ ሆይ! በአገልጋይህ ውስጥ አደራህን እንዳስቀምጥክና ይህም ለዓለም ሕይወት የሰጠህበት መንፈስ መሆኑን እመሠክራለሁ።

በቀናትህ የፈጸመውን ሥራ ምሕረት በተመላበት ሁኔታ እንድትቀበለው በግልጸትህ ሉል ብርሃን እለምንሃለሁ። በመልካም ፈቃድህ ክብር እንዲጎናጸፍና በአንተ ተቀባይነት እንዲያገኝ ፈቃድህ ይሁን።

ጌታዬ ሆይ! አቤቱ አንተ የሰዎች ሁሉ ጌታ ሆይ! እኔ ራሴና የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ስለ ኃያልነትህ እንመሠክራለን፡ ይህን ወደ አንተ፡ ወደ መንግሥተ ሰማያዊ ሥፍራህ፡ ወደ ላቀው ገነትህና ወደ ቅርበትህ ማረፊያ ያረገውን መንፈስ ከአንተ ከራስህ እንዳታገልለው እለምንሃለሁ።

አምላኬ ሆይ፡ አገልጋይህ ብዕር ሊገልጻቸው እንደበትም ሊያወሳቸው በማይችል መንግሥተ ሰማያዊ ሥፍራዎች ውስጥ ከሕሩያንህ፡ ከቅዱሳንህና ከመልእክተኞችህ ጋር እንዲወዳጅ ፈቃድህ ይሁን።

ጌታዬ ሆይ፡ በእውነቱ ምስኪኑ ወደ ሀብትህ መንግሥት፡ ባይተዋሩ በክልሎችህ ውስጥ ወዳለው መኖሪያ ቤቱ፡ እርሱ በጣም የተጠማው ወደ በረከትህ

መንግሥተ ሰማያዊ ወንዝ ገሥግሿል:: ጌታ ሆይ: ከጸጋህ ማዕድና ከበረከትህ ችሮታ ድርሻውን አትንፈገው:: አንተ በእውነቱ ፍጹም ኃያሉ: ጸጋ የተመላው:ፍጹም በረከት የተመላው ነህና!

አምላኬ ሆይ: አደራህ ወደ አንተ ተመልሷል:: አሁን አቀባበል ላደረግህለት እንግዳህ ስጦታዎችህንና ችሮታዎችህን : ከጸጋህም ዛፍ ፍሬዎች መለገሱ በምድርና በሰማይ የሚገኙ ግዛቶችህን ከከበበው ጸጋህና በረከትህ የሚጠበቅ ነው:: አንተ የፈቀድከውን ለማድረግ ሥልጣን አለህ:: ከአንተ ጸጋ ከተመላው:ከሁሉም በላይ በረከት ከተመላው: ከሩኅሩኅ: ከለጋሱ: ከይቅር ባዩ: ከክቡሩ: ከሁሉን አዋቂው በቀር ሌላ አምላክ የለም::

ጌታዬ ሆይ: ሰዎች እንግዶቻቸውን እንዲያከብሩ እንዳዘዝካቸው : እርሱ ወደ አንተ ያረገውም በእውነቱ አንተ ዘንድ እንደደረሰና ቅርበትህን እንደተቀዳጀ እመሠክራለሁ:: እንደጸጋህና እንደቸርነትህ ተቀበለው! በክብርህ! አገልጋዮችህን ካዘዝካቸው ተግባር ራስህም ወደ ኋላ እንደማትል: እርሱን በበርከትህ ገመድ ላይ የተንጠላጠለውንና ወደ ሀብትህ ጎሕ ያረገውን እንደማትነፍገው በእርግጥ አውቃለሁ::

ከአንተ ከአንዱ : ከአንድዬው: ኃይል ከተመላው: ከሁሉን አዋቂው: በረከት ከተመላው በቀር ሌላ አምላክ የለም::



33

ጌታ አምላኬ ሆይ: ክብር ለአንተ ይሁን! እርሱን በዘላለማዊ ሉዓላዊነትህ ኃይል ያከበርከውን አታዋርደው: ወደ ዘለዓለማዊ መቅደስህ እንዲገባ ያደረግኸውንም ከአንተ እንዲርቅ አታድርገው:: አምላኬ ሆይ: እርሱን አንተ በጌትነትህ ጥላ ሥር የከለልከውን ከአንተ አርቀህ ትጥለዋለህን? ፍላጎቴ ሆይ: እርሱን አንተ መሸሻው የነበርከውን ከአንተ ዘንድ ታባርረዋለህን? እርሱን አንተ ከፍ ያደረግኸውን ታዋርደዋለህን? ወይም እርሱን አንተን ለማስታወስ ያስቻልከውን ትረሳዋለህን?

አንተ የተከበርክ: እጅግ በጣም የተከበርክ ነህ! አንተ ከእምቅድመ ዓለም ጀምረህ የመላው ፍጥረት ንጉሥና ዋና አንቀሳቃሹ የነበርከው ነህ: ለዘላለምም የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ጌታና ወሳኛቸው ሆነህ መኖርህን ትቀጥላለህ:: አምላኬ ሆይ: አንተ የተከበርክ ነህ! ለአገልጋዮችህ ምሕረት መለገስህን ብታቋርጥ: ሌላ ማን ምሕረት ያደርግላቸዋል፡ አንተ ተወዳጆችህን ካልረዳህ: ሌላ ማን ሊረዳቸው ይችላል?

አንተ የተከበርክ: ለመገመት ከሚቻል በላይ የተከበርክ ነህ! አንተ ለእውነተኛነትህ የተወደስክ ነህ: በእርግጥም እኛ ሁላችንም አንተን እናመልካለን፡ አንተ በፍርድህ ግልጽ ነህ: በእውነትም እኛ ሁላችንም ለአንተ እንመሠክራለን:: አንተ በእርግጥ: ለጸጋህ የተወደድህ ነህ:: ከአንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ: በገዛ ራሱ ነዋሪ ከሆንከው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም::

34

አምላኬ ሆይ! አቤቱ አንተ ኃጢአትን ይቅር ባዩ: ስጦታዎችን ሰጪው: ጭንቅንም አጥፊው ሆይ!

በእውነቱ: ሥጋዊ ልብስን ጥለው ወደ መንፈሳዊው ዓለም ያረጉትን ሁሉ ኃጢአት ይቅር ትልላቸው ዘንድ እማጸንሃለሁ::

ጌታዬ ሆይ! ከኃጢአት ሁሉ አንፃቸው: ኃዘናቸውን አስወግድላቸው : ጨለማውንም ወደ ብርሃን ለውጥላቸው:: ወደ ተድላ ገነት እንዲገቡ አድርጋቸው: ፍጹም ንጹህ በሆነው ውሀ እጠባቸው: ከሁሉም በላይ ከፍተኛ በሆነው ተራራ ላይ ያለውን ግርማህንም እንዲያዩ አድርጋቸው::

**የቀብር ጸሎት**

ሟች ወንድ ከሆነ:

35.1

አምላኬ ሆይ! ይህ በአንተና በምልክቶችህ ያመነ: ከአንተ በቀር ከሁሉም ሙሉ በሙሉ የተ-ላቀቀና ፊቱን ወደ አንተ የመለሰ አገልጋይህና የአገልጋይህም ልጅ ነው:: አንተ በእውነቱ ምሕረትን ከሚያደርጉት ሁሉ በላይ መሐሪው ነህ::

አቤቱ አንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር የምትልና ስሕተቶቻቸውን የምትሸፍን አምላክ ሆይ: ከቸርነትህ ሰማይና ከጸጋህ ውቅያኖስ የሚጠበቀውን አድርግለት:: ከምድርና ከሰማይ መፈጠር በፊት ጀምሮ ወደነበረው የላቀ ምሕረትህ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲገባ ፈቃድህ



ይሁን:: ከአንተ ከዘለዓለም ይቅር ባዩ: ከሁሉም በላይ ለጋሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለምና::

ሟች ሴት ከሆነች

35.2

አምላኬ ሆይ! ይህቺ በአንተና በምልክቶችህ ያመነች: ከአንተ በቀር ከሁሉም ሙሉ በሙሉ የተ-ላቀቀችና ፊቷን ወደ አንተ የመለሰች ሴት አገልጋይህና የሴት አገልጋይህም ልጅ ናት:: አንተ በእውነቱ ምሕረትን ከሚያደርጉት ሁሉ በላይ መሐሪው ነህ::

አቤቱ አንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር የምትልና ስሕተቶቻቸውን የምትሸፍን አምላክ ሆይ: ከቸርነትህ ሰማይና ከጸጋህ ውቅያኖስ የሚጠበቀውን አድርግላት:: ከምድርና ከሰማይ መፈጠር በፊት ጀምሮ ወደነበረው የላቀ ምሕረትህ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንድትገባ ፈቃድህ ይሁን:: ከአንተ ከዘላለም ይቅር-ባዩ: ከሁሉም በላይ ለጋሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለምና::

ከሁለቱ ጸሎቶች ለሚች ያታ የሚስማማውን ይድገም:: ከዚህም በኋላ "አላህ አ አብሃ" የሚለውን ሰላምታ ከሚከተሉት ስድስት ጥቅሶች ከእያንዳንዳቸው በፊት አንዳንድ ጊዜ ማለትም ( በድምሩ ስድስት ጊዜ) በመድገም ጥቅሶቹን እያንዳንዳቸውን አሥራ ዘጠኝ ጊዜ በሚከተለው ትደም ተከተል ይድገም:

አላህ-ኡ-አብሃ (አንድ ጊዜ)
በእውነቱ : ሁላችንም እግዚአብሔርን እናመልካለን:: (19 ጊዜ)

አላህ-ኡ-አብሃ (አንድ ጊዜ)
በእውነቱ : ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት እንሰግዳለን:: (19 ጊዜ)

አላህ-ኡ-አብሃ (አንድ ጊዜ)
በእውነቱ : ሁላችንም ሕይወታችንን ለአምላክ ሰጥተናል:: (19 ጊዜ)

አላህ-ኡ-አብሃ (አንድ ጊዜ)
በእውነቱ : ሁላችንም አምላክን እናወድሳለን:: ( 19 ጊዜ)

አላህ-ኡ-አብሃ (አንድ ጊዜ)
በእውነቱ : ሁላችንም ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን::(19 ጊዜ)

አላህ-ኡ-አብሃ (አንድ ጊዜ)
በእውነቱ : ሁላችንም በአምላክ እንታገሣለን :: (19 ጊዜ)



## ለፈተናና ለችግር ጊዜ

36

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ: በጸጋህና በቸርነትህ ኃዘኔን አጥፋ፡ በሉዓላዊነትህና በኃያልነትህ ሥቃዬን አስወግድ:: አምላኬ ሆይ: ኃዘን ከየአቅጣጫው በከበበኝ ጊዜ ፊቴን ወደ አንተ ሳቀና ትመለከተኛለህ:: አቤቱ አንተ የፍጡራን ሁሉ ጌታ: ለሚታዩና ለማይታዩት ነገሮች ሁሉ ጥላና ከለላ የሆንከው ሆይ! ከእነዚያ ፊቶቻችውን ወደ አንተ ከመመለስ ከቶ ምንም ከማያግዳቸው ጋር ትቆጥረኝ ዘንድ: የሰዎችን ልቦችና ነፍሶች በገዛው ስምህ: በምሕረትህ ውቅያኖስ ማዕበልና በጸጋህ የቀኑ ኮከብ ድምቀት እማጠንሃለሁ::

ጌታዬ ሆይ: በቀናትህ የደረሰብኝን አንተ ትመለከታለህ:: አንተን ለማገልገል ለመነሣትና ባሕርያትህን ለማሞገስ የሚያስችለኝን ታገዘልኝ ዘንድ: በእርሱ የስሞችህ ጎሕና የባሕርያትህ የንጋት ሥፍራ በሆነው እማጠንሃለሁ:: አንተ በእውነቱ ፍጹም ኃያሉ: ከሁሉም በላይ ኃይል የተመላው: የሰዎችን ሁሉ ጸሎት ሰሚው ነህና::

በመጨረሻም ተግባሬን ሁሉ ትባርክልኝ: ከኃጢአቴም ታነፃኝ: ፍላጎቴንም ታሟላልኝ ዘንድ በገጽህ ብርሃን እለምንሃለሁ:: አንተ ለሥልጣንህና ለገዥነትህ እያንዳንዱ አንደበት የመሰከረልህ: እያንዳንዱ የሚገነዘብ ልብ ስለ ግርማህና ስለ

ሉዓላዊነትህ ያወቀልህ ነህና:: የጠየቁህን ከምትሰማው: መልስም ለመስጠት ከማትቆጠበው፡ ከአንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም::

37

ከእግዚአብሔር በስተቀር ችግርን የሚያስወግድ አለ ወይ? በል:- ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው! እርሱ አምላክ ነው! ሁሉም አገልጋዮቹ ናቸው፡ ሁሉም በትእዛዙ ይኖራሉ::

38

አቤቱ፡ አንተ በመከራዬ ጊዜ ማረፊያዬ! በጭንቀቴም ጊዜ ጋሻዬና መከታዬ ! በችግር ጊዜ መጠጊያዬና መሸሻዬ! በብቸኝነቴም ጊዜ ባልደረባዬ ! በኀዘኔ ጊዜ መጽናኛዬ! በጓደኛ-ቢስነቴም ጊዜ አፍቃሪ ጓደኛዬ! የኀዘኔን ሥቃይ የምታርቅ ኃጢአቴንም ይቅር የምትል ጌታ አምላኬ ሆይ!

በዚህ በመለኮታዊ አንድነትህ ዘመን የአንተን ፈቃድ ከሚቃወም ነገር ሁሉ እንድትከልለኝ: እንከን የሌለብኝና ያልተበከልኩ ሆኜ የጸጋህን ዛፍ ጥላ እንዳልፈልግ እንቅፋት ከሚሆንብኝ ርኩሰት ሁሉ እንድታነጻኝ: ሙሉ በሙሉ ወደ አንተ በመዞር በሙሉ ልቤ: አዕምሮዬና አንደበቴ በጋለ ስሜት እማጸንሃለሁ::

ጌታ ሆይ : በደካማው ላይ ምሕረት ይኑርህ: በሽተኛውንም ፈውስ: የሚያቃጥለውንም ጥም አርካ::



የፍቅርህ እሳት የሚጋጋ፣ በትን ልብ ደስ አሰኘው÷ በመንግሥተ ሰማያዊ ፍቅርህና መንፈስህ ነበልባል አንድደው::

የመለኮታዊ አንድነት መቅደሶችን በቅድስና ካባ አጎናጽፋቸው÷ የቸርነትህንም ዘውድ በራሴ ላይ ድፋልኝ::

ፊቴን በጸጋህ ሉል ብርሃን አብራልኝ÷ በቅድስናህም ደጀሰላም አገልግል ዘንድ በቸርነትህ እርዳኝ::

ልቤ ለፍጡራንህ በሚኖረው ፍቅር እንዲጥለቀለቅ አድርገው፤ የምሕረትህ ምልክት÷ የጸጋህ መታወቂያ÷ በተወዳጆችህ መካከል ስምምነት አስፋፊ÷ ለአንተ ያደርኩ÷ ያንተን ትዝታ የማወሳ÷ ራሴንም ረስቼ ያንተ የሆነውን ሁሉ የማስታውስ እንድሆን ፈቃድህ ይሁን::

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ÷ የይቅርታህንና የጸጋህን ልዝብ ነፋስ አታርቅብኝ ፤ ከረዳትነትህና ከፍቅርህ ምንጭ አትንሳኝ::

በጠባቂ ክንፎችህ ጥላ ሥር እንዳርፍ ፍቀድልኝ÷ የፍጹም ጠባቂ ዓይንህን እይታ አሳርፍብኝ::

ስምህን በሕዝብህ መካከል እንዳወድስ÷ ድምጼም በታላላቅ ጉባዔዎች ላይ ከፍ እንዲል÷ ከከናፍሮቼም የአንተ ምስጋና ጎርፍ እንዲፈስ ምላሴን አፍታታ::

አንተ በእውነቱ÷ ጸጋ-የተመላው÷ የተመሰገነው፡ ኃያሉ÷ ምንም የማይሳነው ነህና!

39

(በሴት የሚደረግ)

ጌታዬ ፡ ተወዳጄ ፡ ፍላጎቴ ሆይ! በብቸኝነቴ ጊዜ ተጎዳኘኝ፡ በማዞቴም ጊዜ አብረኸኝ ሁን:: ኃዘኔን አስወግድልኝ፡ ለውበትህም ያደርኩ አድርገኝ፡ ከአንተ በስተቀር ከሌላው ነገር ሁሉ አግልለኝ፡ በቅድስናህም መዓዛ ወደ አንተ ሳበኝ:: በመንግሥትህም ውስጥ ውሉዬን ከእነዚያ ከአንተ በስተቀር ከሌላው ነገር ሁሉ ከተላቀቁት፡ የአንተንም ቅዱስ ደጀሰላም ለማገልገል ከሚናፍቁትና በእምነትህ ከጸኑት ጋር እንድጎዳኝ አድርገኝ:: ለመልካም ፈቃድህ ከበቁት ሴት አገልጋዮችህ አንዷ ለመሆን አስችለኝ:: በእውነቱ አንተ ጸጋ የተመላው፡ ለጋሱ ነህና::

<u>ለጽናት</u>

40

ስምህ የተከበረ ይሁን አምላኬ ሆይ! ለአንተ ባለን ፍቅርና ለፈቃድህ በታዛዥነታችን ለመጽናት፡ እይታዎቻችንን በአንተ ፊት ላይ ለማተኮርና ክብርህን ለማወደስ እንድታስችለን፡ የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ በከበበው ሥልጣንህ፡ ከመላው ፍጥረት ልቆ በሚገኘው ሉዓላዊነትህ፡ በጥበብህ ውስጥ በተደበቀውና ምድርህንና ሰማይህን በፈጠርክበት ቃልህ እማጠንሃለሁ:: አምላኬ ሆይ፡ የአንተን ምልክቶች በፍጡራንህ መካከል በሰፊው ለማሰራጨት፡ በመንግሥትህም ውስጥ እምነትህን ለመጠበቅ



የሚያስችለንን ኃይል ስጠን:: ከፍጡራንህ መካከል ማንኛውም ስምህን ሳያነግ ራስህን ችለህ ዘለዓለም ኖረሃል:: ከእምቅድመ ዓለም ጀምረህ በነበርክበት ሁኔታ ዘለዓለም ትኖራለህ::

ፍጹም እምነቴን በአንተ አኑሬአለሁ፡ ፊቴንም ወደ አንተ መልሼአለሁ፡ በፍቅራዊ ጥበቃህ ገመድ ላይ ተንጠላጥያለሁ፡ ወደ ምሕረትህም ጥላ ገስግሼአለሁ:: አምላኬ ሆይ፡ ተስፋው እንደተቀጨበት ሰው ከደጅህ አውጥተህ አትጣለኝ፡ አንተን ብቻ ስለምሻ ጸጋህን አትንሳኝ:: ከአንተ ከዘለዓለም ይቅር-ባዩ፡ ከሁሉም በላይ ለጋሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለምና::

አቤቱ ላወቁህ ሁሉ ተወዳጅ የሆንከው ሆይ ፡ ለአንተ ምስጋና ይድረስህ!

41

የጸጋና የምሕረት ጌታ የሆንክ አምላኬ ሆይ! አንተ በትእዛዝ ቃሉ መላው ፍጥረት ወደመኖር የተጠራበት ንጉሥ ነህ፡ የአገልጋዮቹ ተግባሮች ጸጋውን ከመለገስ ያልገቱት፡ የቸርነቱንም መገለጽ ሊያስቀሩ ያልቻሉት ፍጹም ቸር ጌታ ነህ::

ይህ አገልጋይህ በዓለሞችህ እያንዳንዱ ዓለም የደህንነቱ ምክንያት የሆነውን እንዲያገኝ ታደርገው ዘንድ እማጸንሃለሁ:: አንተ በእውነቱ ፍጹም ኃያሉ፡ ከሁሉም በላይ ኃይል የተመላው፡ ሁሉን አዋቂው፡ ፍጹም ጠቢቡ ነህና::

## 42

ከሁሉም በላይ ተወዳጁ የሆንክ ጌታ ሆይ÷ ምስጋና ለአንተ ይሁን! በእምነትህ ጽኑ አድርገኝ÷ ከእነዚያ ቃል- ኪዳንህን ካልጣሱት÷ የራሳቸውን ከእውነት የራቁ ከንቱ እምነቶችና ጣዖቶች ካልተከተሉትም ጋር እንድቆጠር ፈቃድህ ይሁን:: በአንተ ዘንድ የእውነት መቀመጫ ለማግኘት አስችለኝ÷ የምሕረትህንም ምልክት አጎናጽፈኝ÷ ከእነዚያም ምንም ፍርሐት ከማይኖርባቸው÷ በኃዘንም ላይ ከማይጣሉት አገልጋዮችህ ጋር እንድቀላቀል አድርገኝ:: ጌታዬ ሆይ÷ ለራሴ አትተወኝ÷ እርሱን የአንተ የራስህ ክስተት የሆነውን ከማወቅ አትንፈገኝ÷ ከእነዚያ ከአንተ ቅዱስ መንበር ፊቶቻቸውን ከአዞሩትም ጋር አትቁጠረኝ:: አምላኬ ሆይ÷ ከእነዚያ ውበትህን አትኩረው ለማየት ከታደሉት÷ በዚያም ትርዒት ደስታን የሚደሰቱ በመሆናቸው÷ የዚያችን ትንሽ[illegible]ን ጊዜ እንኳ÷ በሰማያትና በምድር መንግሥታት ግዛት ወይም በመላው ፍጥረተ ዓለም ከማይለውጡት ጋር ቁጠረኝ:: ጌታ ሆይ÷ የምድርህ ሕዝቦች በአሳዛኝ ሁኔታ በተሳሳቱባቸው በእነዚህ ቀናት÷ በእኔ ላይ ምሕረት ይኑርህ፣ አምላኬ ሆይ÷ ስለዚህ ያንን በአንተ አስተሳሰብ ተገቢ የሆነውን ለግሰኝ:: በእውነቱ አንተ ፍጹም ኃይል የተመላው÷ ጸጋ የተመላው÷ በረከት የተመላው÷ ዘለዓለም ይቅር-ባዩ ነህና::

አምላኬ ሆይ÷ ከእነዚያ ጆሮዎቻቸው ከደነቆሩት÷ ዓይኖቻቸው ከታወሩት÷ አንደበቶቻቸው ንግግር አልባ ከሆኑት÷ ልቦቻቸውም መገንዘብ



ከተሳናቸው ጋር እንዳልቆጠር ፈቃድህ ይሁን:: ጌታ ሆይ÷ ከድንቁርናና ከራስ ወዳድነት ፍላጎት እሳት አድነኝ÷ ወደ ላቀው ምሕረትህም ክልል እንድገባ አድርገኝ፡ ያንን ለሕሩያንህ ያዘዝከውንም በላዬ አውርድልኝ:: የፈለግኸውን ለማድረግ ችሎታ ያለህ ነህና:: በእውነቱ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ÷ በገዛ ራሱ ነዋሪው ነህ::

## 43

አቤቱ አምላክ ሆይ÷ የተመሰገንክና የተወደስክ ነህ! ወደ ቅዱስ ቅርበትህ የመድረስ መቀዳጃው ቀን በፍጥነት እንዲቃረብ ፈቃድህ ይሁን:: በፍቅርህና በመልካም ደስታህ ኃይል ልቦቻችንን አስደስትልን÷ ለፍላጎትህና ለትእዛዝህም በፈቃደኛነት እንድንገዛ ጽኑነትን አጎናጽፈን:: በእውነቱ ዕውቀትህ የፈጠርካቸውንና የምትፈጥራቸውን ነገሮች ሁሉ ያቅፋል፡ የመንግሥተ ሰማይ የሆነው ኃያልነትህም ወደ መኖር ከጠራኸውና ከምትጠራው ከማንኛውም ነገር ይልቃል:: ከአንተ በቀር የሚሰገድለት ማንም የለም፡ ከአንተ በቀር የሚፈለግ ማንም የለም፡ ከአንተ በቀር የሚመለክ ማንም የለም፡ ከበጎ ፈቃድህም በቀር ምንም የሚወደድ የለም::

በእውነቱ አንተ ከሁሉ በላይ ከፍተኛው ገዢ÷ የላቀው እውነት፡ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፡ በገዛ ራሱ ነዋሪው ነህና::

44

ጌታ አምላኬ ሆይ! ተወዳጆችህ በእምነትህ እንዲጠነክሩ፡ በመንገድህ እንዲራመዱ፡ በሃይማኖትህ እንዲጸኑ እርዳቸው። እኔነትንና የብርቱ ስሜት ውርጂብኝ ወረራን ለመቋቋምና የመለኮታዊ መርሐን ብርሃን ለመከተል የሚያስችላቸውን ጸጋህን ስጣቸው። አንተ ኃይል የተመላው፡ ጸጋ የተመላው፡ በገዛ ራሱ ነዋሪው፡ ለጋሱ፡ ሩኅሩኁ፡ ፍጹም ኃያሉ፡ ፍጹም በረከት የተመላው ነህና።

ጸሎተ ትምሕርት

45

ጌታ አምላኬ ሆይ፡ ምስጋና ለአንተ ይሁን! ማንም ሰው በሚገባ ባላወቀው፡ ታላቅነቱንም ማንም ነፍስ ባልተረዳው ስምህ እማጸንሃለሁ፡ ልቤን የፍቅርህና የትውስታህ ማኅደር እንድታደርግልኝ፡ በእርሱ የግልጸትህ ምንጭና የምልክቶችህ ጎሕ በሆነው እማጸንሃለሁ። እንዲሁም ከዚህ ከልቤ የጥበብህ የሕይወት ውሀዎች፡ የውዳሴህና የምስጋናህ ንጹህ ጅረቶች ይወርዱ ዘንድ፡ ከታላቁ ውቅያኖስህ ጋር አገናኘው።

የአካሌ መለያልዮች ስለአንድነትህ ይመሠክራሉ፡ የእራሴ ፀጉርም ስለሉዓላዊነትህና ስለታላቅነትህ ኃይል ያውጃል። ራሴን ፍጹም ዝቅ በማድረግና ሙሉ በሙሉ በመርሳት በጸጋህ በር ላይ ቆሜአለሁ፡ በቸርነትህም ካባ



ጠርዝ ላይ ተንጠላጥያለሁ፡ የዓኖቼንም እይታ ወደ ስጦታዎችህ አድማስ መልሼአለሁ።

አምላኬ ሆይ፡ ለግርማህ ታላቅነት የሚገባውን ዕድል ወስንልኝ፡ ሙታንም ከመቃብሮቻቸው በፍጥነት በመውጣትና እምነታቸውን ሙሉ በሙሉ በአንተ ላይ በመጣል፡ የእይታቸውንም ትኩረት ወደ እምነትህ አቅጣጫና ወደ ግልጸትህ የንጋት ሥፍራ በመመለስ ወደ አንተ በፍጥነት እንዲገሰግሱ እምነትህን እንዳስተምር፡ በሚያጠናክረው ጸጋህ እርዳኝ።

አንተ በእውነቱ፡ ፍጹም ኃይል የተመላው፡ ፍጹም ከፍተኛው ፡ ሁሉን አዋቂው፡ ፍጹም ጠቢቡ ነህና።

46

አምላኬ ሆይ! የአገልጋዮችህ ጉዳይ ሁሉ እንዲሰምር ከተሞችህም እንዲያብቡ ለማድረግ እንድችል ትረዳኝ ዘንድ ፡ ከሁሉም በላይ በተከበረው ስምህ እለምንሃለሁ። አንተ በእውነቱ፡ በሁሉም ነገሮች ላይ ሥልጣን ያለህ ነህና።

47

(በሴት የሚደረግ)

አቤቱ አንተ እጅግ ተወዳጄ ሆይ! በሕግ ተላላፊዎች ክባድ ወረራም ሆነ በከሃዲዎች ቁጣ በማናወላውልበት ሁኔታ ስምህን ከፍ ከፍ ለማድረግ፡ መልእክትህን ለማስተላለፍና እምነትህን ለማወጅ እንድንችል፡ እኔንም አገልጋዮችህንም በጸጋህ እንድትረዳን፡ ሰላም ማጣትን ወደ እርጋታ፡ ፍርሐትን ወደ ልበ ሙሉነት፡ ድክመትን ወደ ብርታት፡

ውርደትንም ወደ ክብር በምትለውጥበት ስምህ እማጸንሃለሁ::

ጌታዬ ሆይ! እኔ ወደ አንተ ጥሪ ያዳመጥኩ፥ ወደ አንተም ለመቅረብ የፈጠንኩ፥ ከራሴም በመሸሽ ልቤን በአንተ ላይ ያሳረፍኩ ሴት አገልጋይህ ነኝ:: ጌታዬ ሆይ፥ ከእነዚያ በአንተ ባላመኑትና የአንተን እውነት በአስተባበሉት ሰዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ከሚሰነዘረው ሃሳብ እንድትመክተኝ፥ ከውስጡ የምድር ሀብቶች ሁሉ እንዲመጡ በተደረጉበት ስምህ እማጸንሃለሁ::

አንተ የሚያስደስትህን ለማድረግ ኃይል የተመላው ነህ:: አንተ በእውነቱ ሁሉን አዋቂው ፍጹም ጠቢቡ ነህ::

48

ተወዳዳሪ የሌለህ አምላክ ሆይ! አቤቱ አንተ የመንግሥቱ ጌታ ሆይ! እነዚህ ነፍሶች መንግሥተ ሰማያዊ ሠራዊትህ ናቸው:: እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ጦር ኃይል በመሆን በእግዚአብሔር ፍቅርና በመለኮታዊ ትምህርት ውጋገን እነዚህን ሀገሮች ያስገብሩ ዘንድ በከፍተኛው የሰማይ ሠራዊት ቡድኖች እርዳቸው::

አምላክ ሆይ! ድጋፍና እርዳታ ሁንላቸው፡ በመንግሥትህ ኃይልና በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ድምጻቸውን ያሰሙ ዘንድ፡ በምድረ በዳ፡ በተራራ፡ በሸለቆ፡ በጥሻ፡ በሜዳና በባሕር አለኝታ ሁናቸው::

በእውነቱ፡ አንተ ኃይል የተመላው፡ ኃያሉና ምንም የማይሳነው ነህና፡ እንዲሁም አንተ ጠቢቡ፡ ሁሉን ሰሚውና የሚያየው ነህና::



49

አምላክ ሆይ! አምላክ ሆይ! ይህ ከንፈ ሰባራ ወፍ ነው ፡ በረራውም በጣም ዝግተኛ ነው፤ ወደ ብልጽግናና ወደ መዳን ከፍታ ጫፍ ለመብረር እንዲችል፥ በከፍተኛ ሐሴትና ደስታ ወሰን በሌለው ሕዋ ስፋት ውስጥ እንዲከንፍ ፥ በላቀው ስምህ በሁሉም አካባቢዎች ዜማውን እንዲያሰማ፥ በዚህም ጥሪ ጆሮዎችን እንዲያስደስት፥ ዓይኖችም የመርሐን ምልክቶች በማየት እንዲበሩ እንዲያደግ እርዳው!

ጌታ ሆይ! እኔ ረዳት የሌለኝ፥ ብቸኛና ዝቅተኛ ነኝ:: ለእኔ ከአንተ በስተቀር ሌላ ደጋፊ፥ ከአንተ በስተቀር ሌላ ረዳት፥ ከአንተም ሌላ የሚያኖረኝ የለም:: ለአገልግሎትህ አጠናክረኝ፥ በመላእክትህ ሠራዊት እርዳኝ፥ቃልህን በማሰራጨት ተግባሬ ድልን አጎናጽፈኝ፥ በፍጡራንህም መካከል የአንተን ጥበብ እንድለፍፍ አድርገኝ:: በእውነቱ፥ አንተ ለደካሞች ረዳቱ፡ ለዝቅተኞችም ተከላካዩ ነህና፤ በእውነቱም አንተ ኃይል የተመላው፥ ኃያሉና የማይገታው ነህና!

50

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ድቅድቅ ጨለማ አካባቢዎችን ሁሉ መክበቡን፥ ሀገሮችም ሁሉ በሃሳብ ቅራኔ ሰደድ እሳት እየጋዩ መሆናቸውን፥ እንዲሁም በምድር ምሥራቆችና በምዕራቦችዋ ሁሉ እንዴት የጦርነትና የእልቂት እሳት እንደተቀጣጠለ አንተ ታያለህ:: ደሙ እየጎረፈ ነው፥ አስከሬኖችም በመሬት

ላይ ተዘርረዋል፡ የተቀሉ ጭንቅላቶችም በጦር ሜዳ አቧራ ላይ ተጥለዋል።

ጌታ ሆይ! በእነዚህ ደናቁርት ላይ ኃዘኔታ ይኑርህ፡ በምሕረትና በይቅርታ ዓይንም ተመልከታቸው። እነዚህ አድማሱን የሸፈኑት ጥልቅ ደመናዎች ይበተኑ ዘንድ፡ የእውነት ፀሐይ በዕርቅ ጨረሮች ይበራ ዘንድ፡ ይህ ጥልቅ ጨለማ ይወገድ ዘንድ፡ የሰላም ደማቅ ብርሃንም ጮራውን በሁሉም አገሮች ላይ ይፈነጥቅ ዘንድ ይህን እሳት አጥፋው።

ጌታ ሆይ! ሕዝቦችን ከጥላቻና ከጠላትነት ውቅያኖስ አዘቅት አውጣቸው፡ ከዚህም ከማይበገረው ጨለማ አድናቸው። ልቦቻቸውን አስተሳስር፡ ዓይኖቻቸውንም በሰላምና በእርቅ ብርሃን አብራ። ከጦርነትና ከደም መፋሰስ አዘቅት አድናቸው፡ ከስሕተት ጨለማም ነፃ አውጣቸው። ግርዶሹን ከዓይኖቻቸው ግለጥላቸው፡ ልቦቻቸውንም በመርሖ ብርሃን አብራ። በአዛኝ ምሕረትህና ርኅራኄህ ያዛቸው እንጂ ፡ የኃያሎቹን ቅልጥሞች እንኳ በሚያንቀጠቅጠው በአንተ ፍትሕና በቁጣህ አትፍረድባቸው።

ጌታ ሆይ! ጦርነቶች ተራዝመዋል። ጭንቀትና ሥጋት ተባብሰዋል፡እያንዳንዱም ለምለም አካባቢ ወደ ጠፍንት ተለውጧል።

ጌታ ሆይ! ልቦች አዝነዋል፡ ነፍሶችም ተጨንቀዋል። በእነዚህ ምስኪኖች ነፍሶች ላይ ምሕረት ይኑርህ እንጂ፡ ራሳቸው ለሚመኙት ከመጠን ያለፈ ፍላጎት አትተዋቸው።



ጌታ ሆይ! ፊቶቻቸው በመርሖ ጨረር የበሩ፡ ከዓለም የተላቀቁ፡ ስምህን የሚያወድሱ፡ የአንተን ምስጋና የሚናገሩ፡ በሰውም ዘር መካከል የቅዱስነትህን መዓዛ የሚያሰራጩ ትሑታንና ታዛዦች ነፍሶችን በአገሮችህ ሁሉ ውስጥ አስነሣ።

ጌታ ሆይ! ጀርባዎቻቸውን አጠንክር፡ ሽንጦቻቸውን ደግፍ፡ ከሁሉም በላይ ታላቅ በሆኑት በፍቅርህ ምልክቶችም ልቦቻቸውን አስደስት።

ጌታ ሆይ! በእውነቱ እነርሱ ደካሞች ናቸው፡ አንተ ግን ብርቱውና ኃያሉ ነህ፡ እነርሱ አቅመቢሶች ናቸው፡ አንተ ግን ረዳቱና መሐሪው ነህ።

ጌታ ሆይ! የአመጽ ውቅያኖስ እየሞገደ ነው፡ ሁሉንም አካባቢዎች ባቀፈው ወሰን በሌለው ጸጋህ በስተቀር እነዚህ ኃይለኛ ነፋሶች አይረጉም።

ጌታ ሆይ! በእውነቱ ሕዝቦች በከፍተኛ መድረዊ ምኞት አዘቅት ውስጥ ናቸው፡ ወሰን ከሌለው ልግሥናህም በስተቀር ምንም ነገር ሊያድናቸው አይችልም።

ጌታ ሆይ! የእነዚህን የእርኩስ ምኞቶች ጨለማ አስወግድ፡ ሀገሮችም ሁሉ በቅርብ ጊዜ በሚበሩበት በፍቅርህ ፋኖስ ልቦችን አብራ። እነዚያን፡ ለውበትህ ፍቅር ሲሉ፡ አገሮቻቸውን ቤተሰቦቻቸውንና ልጆቻቸውን ጥለው፡ መዓዛዎችህን ለማሰራጨትና ትምህርቶችህን ለማስፋፋት፡ ወደ ውጭ አገሮች የሚጓዙትን ተወዳጆችህን አጠንክራቸው። በብቸኝነት ጊዜአቸው ጓደኛ፡ በባዕድ አገር ረዳታቸው፡ የኀዘናቸው አስወጋጅ፡ በመከራ ጊዜ አጽናኝ

ሁንላቸው:: ለጥማታቸው የሚያረካ መጠጥ፥ ለበሽታቸው ፈዋሽ መድኃኒት ፥ የልቦቻቸው ስሜት ነበልባል አብራጅ ቅባት ሁን::

በእውነቱ፥ አንተ ከሁሉም በላይ ለጋሱ፥ ወሰን የሌለው ጸጋ ባለቤት ነህ፥ እንዲሁም፥ አንተ ሩኅሩኁና መሐሪው ነህና::

51

አቤቱ አንተ ቸር ጌታ ሆይ! የመርሐን አውራ ጎዳና ስለአሳየኸን፥ የመንግሥትህን በሮች ስለከፈትክልንና ራስህንም በእውነት ፀሐይ አማካይነት ስለከሰትክልን ምስጋና ለአንተ ይሁን:: ለዕውራን ማየትን ሰጥተሃል፤ ለደንቆሮዎች መስማትን አድለሃል፤ ሙታንን አስነስተሃል፤ ድሆችን አበልጽገሃል፤ መንገድ የሳቱትን መንገዱን አሳይተሃቸዋል፤ እነዚያን ከንፈሮቻቸው የደረቁትን ወደ መርሐ ምንጭ መርተሃቸዋል፤ የተጠሙትንም ዓሶች ወደ እውነት ውቅያኖስ እንዲደርሱ አድርገሃል፤ የሚንከራተቱትንም ወፎች ወደ ጸጋ የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ ጋብዘሃል::

አቤቱ አንተ ፍጹም ኃያል ሆይ! እኛ ባሮችህና ምስኪኖችህ ነን:: እሩቅ ነንና የአንተን ቅርበት እንሻለን፤ ለምንጭህም ውሀ እንጠማለን፤ ሕሙማን ነንና ፈውስህን እንናፍቃለን:: በመንገድህ እንጓዛለን፤ ነፍሶች ሁሉ "አምላክ ሆይ፥ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ምራኝ" የሚለውን ጩኸት ያሰሙ ዘንድ፥ መዓዛህን ከማሰራጨት በስተቀር ሌላ ዓላማና ተስፋ የለንም:: ብርሃኑን ለማየት ዓይኖቻቸው እንዲከፈቱ፥



ከድንቁርና ጨለማ ነፃ እንዲወጡ፡ በመሪነትህም ፋኖስ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ፡ ቁራሽ ቢሶች ድርሻቸውን እንዲቀበሉ፡ የተገለሉትም ሁሉ የምሥጢሮችህ ተካፋዮች እንዲሆኑ ፈቃድህ ይሁን::

ፍጹም ኃያል ሆይ! በምሕረትህ አስተያየት ተመልከተን:: መንግሥተ ሰማያዊ ማረጋገጫን አድለን:: ለአገልግሎትህ እንዲረዳንና እንደ አንጸባራቂ ከዋክብት የመርሐህን ብርሃን በእነዚህ ክፍለ ሀገሮች እንድናበራ የመንፈስ ቅዱስን እስትንፋስ አጎናጽፈን::

አንተ በእርግጥም ብርቱው፡ ኃያሉ፡ ጠቢቡና የሚያየው ነህና::

ለአቅኚዎች::

52

አምላክ ሆይ፡ የአንተን መልካም ደስታ ከመቀዳጀት፡ ለአንተ አገልጋይ ለመሆን ተቀባይነት ስለማግኘቱ ማረጋገጫን ከማግኘት፡ ለአንተ አገልግሎት ለማበርከት ዓላማ ራሴን ከመስጠት፡ በአንተ ታላቅ የወይን እርሻ ውስጥ ከመሥራትና ሁሉንም ነገር በአንተ መንገድ መስዋዕት ከማድረግ በስተቀር በልቤ ውስጥ ምንም ዓይነት ሌላ ፍላጎት እንደሌለ አንተ የምታውቀውና ምሥክሬም ነህ:: አንተ ሁሉን አዋቂው፡ ሁሉን የሚያየው ነህና:: ለአንተ ካለኝ ፍቅር፡ እርምጃዎቼን ወደ ተራሮችና ወደ በረሃዎች በማቅናት፡ የአንተ መንግሥት ስለመምጣቱ ክፍ ባለ ድምጽ ከማወጅ፡ በሰዎችም ሁሉ መካከል ጥሪህን ከማሰማት በስተቀር ሌላ ምኞት

የለኝም:: አምላክ ሆይ! ለዚህ ረዳት ለሌለው መንገዱን ክፈትለት፡ ለዚህ ሕመምተኛ መድኃኒት ፍቀድለት፡ ለዚህም ለሚሰቃየው ፈውስህን አውርድለት:: ልቤ እየነደደ፡ ከዓይኖቼም እንባ እየጎረፈ በአንተ ደጀሰላም ላይ ሆኔ እማጸንሃለሁ::

አምላኬ ሆይ! በመንገድህ ማንኛውንም መከራ ለመቻል ዝግጁ ነኝ፥ በሙሉ ልቤና ነፍሴም ማንኛውንም ችግር ለመቋቋም እመኛለሁ::

አምላክ ሆይ! ከፈተናዎች ጠብቀኝ:: እኔ ከሁሉም ነገሮች ፊቴን ማዞሬንና ራሴን ከሁሉም ሃሣቦች ነፃ ማድረጌን አንተ ደህና አድርገህ ታውቃለህ:: አንተን ከማንሳት በስተቀር ምንም ሥራ፡ አንተን ከማገልገልም ቢቀር ሌላ ምንም ምኞት የለኝም::

<u>ለእምነት፡ ድል</u>

53

ጌታ አምላኬ ሆይ፡ ስምህ የተወደሰ ይሁን! ጨለማ እያንዳንዱን አገር ሸፍኗል ፡ የክፋት ኃይሎችም የሁሉንም አገር ሕዝቦች ከበዋል:: ይሁን እንጂ ፡ በእነዚህ ውስጥ የጥበብህን ውበቶች አያለሁ፡ የአምላካዊ ጥበቃህንም ብርሃኖች ድምቀት እለያለሁ::

እነዚያ ልክ በግርዶሽ የተሸፈኑ ያህል ከአንተ የተዘጉት፥ የአንተን ብርሃን ለማጥፋት፡ እሳትህን ለማዳፈን፡ የጸጋህም ነፋሶች እንዳይነፍሱ ለመገደብ ኃይል አለን በለው ያስባሉ:: አይቻላቸውም፡ ለዚሁም



የአንተ ታላቅነት ይመሰክርልኛል! እያንዳንዱ መከራ የጥበብህ ማኅደር ፥ እያንዳንዱም ስቃይ የአምላካዊ ጥበቃህ መጓጓዣ ስለሆነ እንጂ ፡ የምድርና የሰማይ ኃይሎች ሁሉ ቢያብሩብንም እንኳ፥ ማንም ደፍሮ ባልተቃወመን ነበር:: በፊቴ በግልጽ የተዘረጉትን የጥበብህን ድንቅ ምሥጢራት ሁሉ ብገልጽ ኖሮ፥ የጠላቶችህ ልቧም ዛቦች በተበጣጠሱ ነበር::

ስለዚህ ፥ አምላኬ ሆይ፡ ምስጋና ለአንተ ይሁን! እነዚያን የሚወዱህን ከፈቃድህና ከበጎ ፍላጎትህ በሚጎርፈው ሕግ ዙሪያ እንድትሰበስባቸው፥ ለልቦቻቸውም እርግጠኝነትን የሚሰጠውን እንድትልክላቸው፡ ከሁሉም በላይ ታላቅ በሆነው ስምህ እማጸንሃለሁ::

አንተ የሚያስደስትህን ሁሉ ለማድረግ የማይሳንህ ነህ :: በእውነቱ፡ አንተ በአደጋ ጊዜ ረዳቱ፥ በገዛ ራሱም ነዋሪው ነህ::

54

አምላኬ ሆይ፡ የቀናት ንጉሥ የሆነውን ቀን፥ አንተ ከሁሉ በላቁት መልእክቶችህ ውስጥ ለሕሩያንህና ለነቢያትህ የተስፋ ቃል ያበሰርክለትን ቀን፡ የስሞችህን ሁሉ ክብር ውበት በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ ያበራህበትን ቀን ስለገለጽህ ስምህ የተመሰገነ ይሁን:: ወደ አንተ የተመለሰ፥ አንተ ወዳለህበት የገባ፥ የድምጽህንም ዜማዎች የሰማ ቡራኬው ታላቅ ነው::

ጌታዬ ሆይ፡ የግልጸትህ የላቁ ሐሴቶች የምድርህን ነዋሪዎች ሁሉ ነፍሶች ይሞሉ ዘንድ ፥

እነዚያ ለአንተ ውድ የሆኑት ቃልህን በአገልጋዮችህ መካከል እንዲያወድሱ፡ ምስጋናህንም በፍጡራንህ መካከል እንዲያሰራጩ እንድትረዳቸው፡ በእርሱ፡ የስሞችህ መንግሥት በማምለክ በሚከበው ስም እማጸንሃለሁ።

ጌታዬ ሆይ፡ ወደ ጸጋህ የሕይወት ውሃዎች ስለመራሃቸው፡ በችሮታህ፡ ከአንተ እንዳይከለከሉ ፈቃድህ ይሁን፡ ወደ ዙፋንህም መኖሪያ ስለጠራሃቸው፡ በፍቅራዊ ደግነትህ፡ ከቅርበትህ እንዳታባርራቸው እለምንሃለሁ። ከአንተ በስተቀር ከማንኛውም ነገር ሙሉ በሙሉ እንዲላቀቁ የሚያደርጋቸውን ላክላቸው፡ የጨቋኞች ማየልም ሆነ፡ የእነዚያ በአንተ ከሁሉም በላይ ክብር የተመላና ከሁሉም በላይ ታላቅ የሆነ ህልውና እናምንም ያሉት ሰዎች የሚያቀርቡአቸው ሃሳቦች ከአንተ ሊከለክሉአቸው በማይችሉበት ሁኔታ ፡ በአንተ ቅርበት ሰማይ ውስጥ እንዲበሩ አድርጋቸው።

55

አቤቱ፡ አንተ የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ በትእዛዝህ ኃይል ወደ መኖር ያመጣህ ጌታ ሆይ፡ ክብር ለአንተ ይሁን!

ጌታ ሆይ! እነዚያን ከአንተ በስተቀር ሌላውን የተውትን እርዳቸው፡ ታላቅ ድልም አቀዳጃቸው። ጌታ ሆይ፡ አገልጋዮችህን ለመርዳት፡ ለማበረታታትና ለማጠናከር፡ ስኬታማም እንዲሆኑ ለማስቻል፡ ለመደገፍ፡ ገናናነትን፡ ክብርንና



ከፍተኛነትን ለማጎናጸፍ፡ ለማበልጸግና በድንቅ ድልም አሸናፊዎች እንዲሆኑ ለማድረግ፡ በሰማይና በምድር፡ በመካከላቸውም ሁሉ የሚገኙትን የመላእክት ሠራዊት ላክላቸው።

አንተ የእነርሱ ጌታ፡ የሰማያትና የምድር ጌታ፡ የሁሉ ዓለማት ጌታ ነህ። ጌታ ሆይ፡ በእነዚህ አገልጋዮችህ ኃይል ፡ ይህን እምነት አጠናክረው፡ በዓለም ሕዝቦች ሁሉ ላይ የበላይነትን እንዲያገኙ አድርጋቸው፡ እነርሱ በእውነቱ ከአንተ በስተቀር ከማንኛውም ነገር ራሳቸውን ያላቀቁ አገልጋዮችህ ናቸው፡ አንተ በእርግጥ የእውነተኛ አማኞች መከታ ነህና።

ጌታ ሆይ፡ በእነርሱ ለዚህ ለማይደፈረው እምነት ታማኝ መሆን አማካይነት፡ ልቦቻቸው በሰማያትና በምድር ፡ በመካከላቸውም ከሚገኘው ከማንኛውም ነገር የበለጠ እየጠነከሩ እንዲሄዱ ፈቃድህ ይሁን ፡ ጌታ ሆይ ፡ በሁሉም የሰው ዘር ያተኮረ እይታ ፊት ኃይልህን ያሳዩ ዘንድ እጆቻቸውን በድንቅ ኃይልህ ምልክቶች አበርታ።

56

ጌታ ሆይ! በመንገድህ ሰማዕትነትን ስለፈለጉ፡ ለታጋሽ አገልጋዮችህ በቀናትህ ተገቢ ድል በመፍቀድ አሸናፊዎች አድርጋቸው። ያንን ለአዕምሮዎቻቸው መጽናናትን የሚያመጣውን፡ ውሳጣዊ ሕያውነቶቻቸው ሐሴት እንዲያደርጉ

የሚያደርገውን፡ ለልቦቻቸው እርግጠኝነትን፡ ለአካሎቻቸውም መረጋጋትን የሚሰጠውንና ነፍሶቻቸውን ወደ አምላክ፡ ከሁሉም በላይ ወደተከበረው ዘንድ ለመውጣት፡ ወደ ላቀው ገነትና አንተ ለእውነተኛ የዕውቀትና የመልካም ተግባር ሰዎች ወደ አዘጋጀሃቸው የክብር አካባቢዎች ለመድረስ የሚያስችላቸውን ላክላቸው። በእውነቱ አንተ ሁሉን ነገሮች ታውቃለህ፤ እኛ ግን አገልጋዮችህ፡ ምርኮኞችህ፡ ባሮችህና ምስኪኖችህ ነን። እግዚአብሔር ጌታችን ሆይ፡ ከአንተ በቀር ሌላ ጌታ አንጠራም፤ አቤቱ አንተ ለዚህ ዓለምና ለሚቀጥለው የምሕረት አምላክ የሆንክ ሆይ፡ ከአንተ በቀር ከሌላ ከማንም ቡራኬዎችን ወይም ጸጋን አንማጸንም። የአንተ መላው ሕያውነት የሀብት፡ የነፃነት፡ የክብር፡ የግርማና የወሰን አልባ ጸጋ ምሳሌ ሲሆን፡ እኛ ግን የድህነት፡ የኢምንትነት፡ የረዳተ-ቢስነትና የጥፋት መገለጫዎች ነን።

ጌታ ሆይ፡ ካማችንን፡ ከዚህና ከሚቀጥለው ዓለም መልካም ነገሮች፡ ከሰማይ ጀምሮ ከዚያ በታች እስካለችው ምድር ከተዘረጉትም ብዙና ልዩ ልዩ ጸጋዎች፡ ከአንተ መሠጠቱ በጣም ወደሚገባው ለውጠው።

በእውነቱ አንተ ጌታችንና የሁሉ ነገሮች ጌታ ነህ። ከአንተ ለሆኑት ነገሮች በመጓጓት ፡ ራሳችንን አሳልፈን ለእጅህ እንሰጣለን።



57

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ከሁሉም በላይ ከፍተኛ በሆነው ተራራ ጫፍ ላይ ባለው ቅዱስ ዛፍ፡- በዚያ *"ምሥራቃዊም ምዕራባዊም ባልሆነው"*[1] ዛፍ ውስጥ ፡ ያንን ነበልባሉ ወደ ሰማይ ሠራዊት እስኪያርግ ድረስ የተንበለበለውን እሳት፡ ከዚያም ነበልባል፡ እነዚያ እውነታዎች የመርሐን ብርሃን የጨበጡትና፡- *"በእውነቱ እኛ በደብረ-ሲና ተራራ ዳገት ላይ እሳት አየን"*[2] በማለት የጮሁለትን የመለኮታዊ ፍቅር እሳት ስላቀጣጠልክ ምስጋና ለአንተ ይሁን።

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ከፍተኛ ነበልባሉ መላዋን ምድር ለማንቀሳቀስ እስኪችል ድረስ፡ ቀን በቀን በተተካ ቁጥር ይህ እሳት እየጨመረ እንዲሄድ አድርግ። አቤቱ አንተ ጌታዬ ሆይ! የፍቅርህ ብርሃን በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ እንዲያበራ አድርግ፡ የዕውቀትህን መንፈስ በሰዎች ነፍሶች ውስጥ ተንፍስ ፡ በአንድነትህ ጥቅሶች ልቦቻቸውን አስደስት። እነዚያን በመቃብሮቻቸው ውስጥ የሚኖሩትን ወደ ሕይወት ጥራቸው፡ ትዕቢተኞችን አስጠንቅቅ፡ ደስታ መላዋን ምድር እንዲያቅፍ አድርግ፡ የጠሩ ውሀዎችን ላክልን፡ በግልጽ ውበቶች በተመላውም ጉባኤ ላ ይ ፡ ያንን *"ከካምፉር ምንጭ የተበረዘውን"*[3] ጽዋ አዙርላቸው።

..........................
1. ቁርአን 24:35
2. ቁርአን 28:29
3. ቁርአን 76:5